# ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማኅበራዊ ሳይንስና ሥነ ሰብእ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ-አማርኛ ትምርት ክፍል ለመሠረታዊ ግዕዝ ማስተማሪያ የተዘጋጀ ሞጁል፡፡

በአዲሴ ያለው

## ምዕራፍ ፩

### ፩. የግዕዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ምንነትና ታሪክ

#### ፩.፩. የቋንቋ ምንነት

ቋንቋ ፍፁም ሰብአዊ የሆነና ደመ ነፍሳዊ ያልሆነ የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ ስሜቱንና ፍላጎቱን የሚያስተላልፍበት ስርዓታዊ ምልክት (symbol) ነው፡፡ ስለ ቋንቋ አመጣጥ ብዙ መላምቶች ተብለዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ሁለቱን እንመለከታለን ፩ኛው ለሰው ልጅ ጥንተ አመጣጥ ዳርዊን እንዳስቀመጠው መላምት ቋንቋ በዝግመተ ለውጥ የመጣ ነው የሚል ሲሆን ፪ኛው ደግሞ የመለኮታዊያን መላምት ነው፡፡ ይህ መላምት በመካከለኛው ዘመን ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ሲሆን በዚህ መላምት አራማጆች እምነትና ትንታኔ መሰረት የሰው ልጅ መግባቢያ ቋንቋ ከፈጣሪ የተሰጠው ሲሆን የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቋንቋም እብራይስጥ ነው የሚል ነው፡፡የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቋንቋ አንድ እብራይስጥ ከሆነ በዓለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች ለምን በዙ ለሚለው ጥያቄም የመለኮታዊ መላምት አራማጆች የባቢሎንን ግንብ ታሪክ በማስረጀነት ያነሳሉ[1]፡፡ ግዕዝ ቋንቋንም ከላይ ለቋንቋ እንደተሰጠው አጠቃላይ መላምት ሁሉ የመላዕክት፣ የአዳም የመጀመሪያ፣ የሴም ዘር ቋንቋ ወዘተ. እያሉ ምሁራን ሲገልጹት ይስተዋላል፡፡ ስለ ግዕዝ ቋንቋ አጠቃላይ እሳቤ ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡

#### ፩.፪. የግዕዝ ምንነት

ግዕዝ የሚለው ቃል ትርጉም በ ‹‹ዕ›› ሲፃፍ ነባር ስም ሲሆን ትርጉሙም የመጀመሪያ፣ ሴማዊ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት እንደሆነ በላይ (፳፻፱:፫፻፴፭)እና ያሬድ (፳፻፯:፬፻፯)ይገልፃሉ፡፡ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ለምሳሌ ጌታቸው ኃይሌ (፳፻፰:፱፻፹፰) ግዕዝ ማለት ጠባይ፣ ልምድ፣ባህል፣ ሁኔታ ፣ አመል ወዘተ. ተደርጎ ይፈታል ይላሉ፡፡

---

[1] ኦ.ዘፍ 11፡1-9 ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች ከምስራቅም ተነስተው በሄዱ ጊዜ በሰናዖር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ በዚያ ተቀመጡ እርስ ብርሳቸውም ኑ ጡብ እንስራ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው የምድርም ስፋት እንደ ጭቃ ሆነላቸው እንዲህም ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንስራ በምድር ላይ ሳንበትንም ስማችን እናስጠራው አሉ እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሰሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ እግዚአብሔርም አለ እነሆ እነሱ አንድ ወገን ናቸው ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፡፡ ይህንንም ለማድረግ ጀመሩ አሁን ያሰቡትን ሁሉ ለመስራት አይከለከሉም፡፡ ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው፡፡

ግእዝ በ‹‹እ›› ሲፃፍ ደግሞ ፩ኛ. የፊደላት የመጀመሪያ ሆሄ ስም ማለት ሲሆን ለምሳሌ ሀ፡ለ፡ሐ፡መ፡ሠ፡ረ ወዘተ መጠርያ ፪ኛ. የንባብ አይነት ምሳሌ ግእዝ ንባብ ፫ኛ የዜማ አይነት(የቅዱስ ያሬድ) ምሳሌ ግእዝ፣ እዝል፣ አራራይ ፬ኛ ግእዝ መጀመሪያ ቀዳሚ ማለትም ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ግዕዝ የሚለውን ቃል ለመጻፍ ከሁለቱ ፊደሎች (እ፣ዕ) አንዱን መጠቀም ይቻላል ምክንያቱም ሁለም ከላይ የተሰጡት ምሳሌዎች ከቋንቋው ጉዳይ ጋር የተያያዘ ፍች ስላላቸው ነው፡፡

## ፩.፫. የግዕዝ ቋንቋ አመጣጥ ታሪክ

ግዕዝ ቋንቋ ለቀዳሚ (ጥንታዊ) ቋንቋዎች እንደሚሰጠው ብያኔ ሁሉ በተለይ ደግሞ የመጀመሪያ ከሚለው የቃሉ ፍካሬ (ትርጓሜ) በመነሳት የመላዕክት ቋንቋ፣ የአዳም የመጀመሪያ ቋንቋ፣ የሴም ዘር ቋንቋ፣ የኩሽ ዘር ቋንቋ እያሉ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ እሳቤ እንደሚገልፁት ከላይ ተመልክተናል፡፡ከነዚህ ምሁራን መካከል ኢትጵያዊው ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የግዕዝ ቋንቋ የሴም ዘር ቋንቋ ሲሆን የሴም ቋንቋ ፊደላትን ግን እግዚአብሔር ሄኖስን እንደ ሙሴ ስቦ ህግና ትዕዛዝን አጉልተው የሚያሳዩ ፳፪ት ፊደላትን ሰጠው ይላሉ፡፡ሄኖስ ማለትም ፍፁም ሰው ስጋ ያለው እና የመሲሁ ጸሀፊ ትዕዛዝ እንደሆነም ያብራራሉ፡፡ለይኩን ብርሃኑ ደግሞ ግዕዝ ጥሬ ትርጉሙ መጀመሪያ፣ አንደኛ ከሁሉ በፊት ቀዳሚ ማለት ነው፡፡ ይህም መላው የዓለም ቋንቋ ለምሳሌ አረብኛ አረቦችን ፣ፈረንሳይኛ ፈረንሳዮችን፣ እንግሊዘኛ እንግሊዞችን ማለትም የቋንቋው ባለቤት ማን እንደሆነ በስማቸው ይመሰክራሉ፡፡ግዕዝ ግን ይህን ልምድና አባባል አይጠብቅም የማን እንደሆነ ስሙ አይገልፅም የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የመጀመሪያው የሰው ልጅ (የአዳም) የአፍ መፍቻ  ቋንቋ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ አጠራርም ልሣነ ሰብእ ይባላል፡፡ለዚህ ሁሉ ማጠቃለያ ግዕዝ የሚለው ቃል በትርጉሙ ለራሱ የመጀመሪያ ቋንቋ ነኝ ሲል ይመሰክራል ይላሉ፡፡

በተጨማሪም ለይኩን ብርሃኑ እና ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጀርመናዊውን ሲደ ጳውሎስንና መዐልም ዮሐንስን ጠቅሰው የዓለም ቋንቋ ሁሉ በየነገዱ ስም ሲጠራ ግዕዝ ብቻ በማንም ነገድ ስም አልተጠራም በራሱ በስሙና በተግባሩ እንጂ ግዕዝ ማለትም አንድ፣ አንደኛ፣ መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ለዚህም ተጨማሪ የሚሆን ማስረጃ ‹‹ ወኮነ ኵሉ ምድር አሐተ ከንፈረ ወአሐደ ነገረ››‹‹የምድር ሰው ሁሉ መግባቢያና መነጋገሪያ ቋንቋ አንድ ነው››፡፡የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎችም አዳምና ልጆቹ ናቸው በማለት ያብራራሉ፡፡

ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያይዞ በዘመናችን ባሉ የቋንቋ ምሁራን በግዕዝ ቋንቋ ሌላው አከራካሪው ጉዳይ ደግሞ ቋንቋው የነገደ ካም ወይስ የነገደ ሴም የሚለው ነው ፡፡ የጥንታዊን መዛግብት (philology) መምህር የሆኑት መምህር ደሴ ቀለብ እነዚህን ምሁራን በሶስት ይከፍሏቸዋል፡፡

ሀ. ግዕዝ የነገደ ካም ቋንቋ ነው የሚሉ ምሁራን

ግዕዝ የነገደ ካም ቋንቋ ነው ከሚሉት ምሁራን የሚመደቡት ኃይሉ ሀብቱ፣አስረስ የኔሰው፣አየለ በከሪ፣ ትርሴስሃ ጥበቡ ወዘተ. ሲሆኑ የሚያቀርቡት አመክንዮ(evidence) ግዕዝ የደቡብ ሴማዊ ልሳን ሳይሆን በአረብ ምድር የመጀመሪያዎቹ አፍሪካዊያን /ኩሻዊያን/ ቋንቋ ነው፡፡ብዙዎቹ የአፍሮ እስያነት ቋንቋዎችም የሚገኙት በአፈሪካ ምድር ስለሆነ ግዕዝ አፍሪካዊ ኩሻዊ ልሳን ነው ይላሉ፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው ምሁራን በተለይ አየለ በከሪ *Ethiopic: An African Writing System--Its history and principles* በተሰኘው መጽሐፋቸው ግዕዝ የኩሽ ቋንቋ ነው፡፡ የመጀመሪያው የሰው ልጅ መገኛ የአፍሪካ ቀንድ ነው፡፡ የአፍረካ ቀንድ የመጀመሪያው የሰው ልጅ መገኛ ብቻ ሳይሆን የስለጣኔም መጀመሪያም ነው፡፡የስልጣኔ አንድ አካል የሆነው የግዕዝ ቋንቋና ስነጽሑፍ መገኛ የኩሽ ዘር መኖርያ የአፍሪካ ቀንድ ነው፡፡ስለዚህ ስልጣኔ ከአፍሪካ ቀንድ ወደ አፍሪካ ከዚያ ህንድ ብሎም አውሮፓ ተስፋፍቷል ይላል፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆን ከኦሮምኛ የተወሰዱ የግሪክ ቃላትን ከዚህ በታች በምሳሌነት ይገልጻል፡፡

Bekerie rarely uses etymology-cum-history for his argumentations. For instances a large portion of his book is devoted to what he calls Geez *siwasiw*, ‘grammar’, which he acknow-ledged as originally meaning ‘ladder’. This is in actuality an anagram of Oromo word wazaza ‘a bier upon which the dead bodies are carried to the grave’ (Tutschek, 1844:153), a symbol of wadaa ‘alliance, oath’ with the deceased. The Oromo and Classical Greek concept of grammar correspond both in form and meaning. In Oromo, the polysemous word qaraa means, among others, ‘read, sharpen; inquire, be wise, civilized’ from which the metaphorical qoro ‘wise, aristocrat, hawk’ comes. The same concept must be at work in Meroitic kerma, qore ‘chief, king’ (Aubin 2003: 31) and Egyptian ‘hawk’ and its symbolic representations. **It is not by chance but by influence of Africans that in Classical Greek *χάra* means ‘pierce, sharpen, engrave,’ the embryonic stage of grammar and grammatology.**

በአጠቃላይ እንደነዚህ ምሁራን እምነት ግዕዝና ሌሎች የኩሽ ቋንቋዎች ለሌሎች ዓለማት መነሻ ናቸው፡፡

### ለ. ግዕዝ የነገደ ሴም ቋንቋ ነው የሚሉ ምሁራን


በግዕዝ ቋንቋ ላይ ምረምር ያደረጉ አብዛኞዎቹ ምሁራን የሚስማሙት ግዕዝ የነገደ ሴም ቋንቋ ነው በሚለው ነው፡፡ከእነዚህ ምሁራን መካከል ምሳሌ እንመልከት ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ ዘርዓ ዳዊት አድሐኖ፣በላይ መኮነን፣ ጌታቸው ኃይሌ፣ ሊኦል ቤንደር፣ ኦገስት ዲሊማን፣ ወልፍ ሌስላው ወዘተ. ሲሆኑ የሚያቀርቡት አመክንዮ ለምሳሌ ጌታቸው ኃይሌ ግዕዝ የሴም ቋንቋዎች ከሚባሉት አንዱ ነው፡፡ተናጋራዎቹ ግን እነማን እንደነበሩ በትክክል ማወቅ አይቻልም ይላሉ፡፡የአብዛኞዎቹን የቋንቋ ምሁራን ሀሳብ ጠቅሰውም አጠቃላይ የሴም ቋንቋ ተናገሪ በቀይ ባህር አካባቢ ይኖር ነበር ይላሉ፡፡የሴም ቋንቋዎች ብለው የሚከፍሏቸው ዐረቢ፣ ደቡብ ዐረቢ (ሳባ)፣ እብራይስጥ፣ ሱርስት፣ አራምኛ፣ እንዲሁም ግዕዝ ናቸው፡፡ እነዚህ ቋንቋዎች ሁሉ አንድ ቤተሰብ (ዘመዳሞች) መሆናቸውን በመልካቸው ማለትም በተመሳሳይ ፊደላቸው፣ ቃላታቸው እንዲሁም በሰዋስው መሰረታቸው እንረዳለን ሲሉ ዝምድናው ግን ምን ዓይነት እንደሆነ ማወቅ አንችልም ይላሉ ምክንያታቸው ደግሞ ተመሳሳይነት ዝምድናን እንጅ የዝምድናው ዓይነት ምን እንደሆነ ስለማያስረዳ ነው፡፡ግዕዝ የነገደ ሴም ነው ከሚሉት አንዱ ወልፍ ሌስላው ደግሞ ግዕዝ ሰሜን ኢትዮ ሴማዊ ላይ የሚመደብ ምንአልባትም በኢትዮጵያ እስከ ፲፪ኛውና ፲፫ኛው መቶ ክ/ዘመን ሊነገር የሚችል ቋንቋ መሆኑን ይገልጻል፡፡ቋንቋው በኢትዮጵያ ለስነጽሑፍና ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ቋንቋ ነው በማለትም ያክላል፡፡

ጀርመናዊው ኦገስት ዲልማን ደግሞ የሚከተለውን ሀሳብ ያክላል፡፡In origin and essence Ethiopic is a pure Semitic speech,transplanted by people who migrated from Yemen to Abyssinia. **Character** -In its sounds and laws of sounds, in its roots, inflectional expedientsand word-forms, in all that is reckoned the structureand essence of a language, it bears throughout a genuine and uncorrupted Semitic stamp (3). All its roots may be pointed out as recurring in the other Semitic languages, especially in Arabic,although often diverging greatly in form, or preserved merely in a fragmentary condition. From the indigenous languages of these African regions only a very few names of plants and animals have been taken; while the names of the months,—which Ludolf imagined to have come from the same stock,—appear to be of decidedly

Semitic origin. True, the Geez people learned a few straythings, about matters so external as writing, from the Greeks, with whom the Abyssinians had dealings in times even before Christ, and with whom they continued in uninterrupted intercourse.

ሐ. ከላይ የተለያዩ ምሁራን ግዕዝ ቋንቋን የሴም ዘር የካም ዘር ቋንቋ እያሉ የተለያየ አመክንዮ ያቅርቡ እንጅ እንደ ደሴ ቀለብ ገለጻ አሁን ያለው የስነ ልሳን ጥናት (linguistics study)ከዘር ሀረግ ይልቅ መልካዐ ምድራዊ አቀማመጥን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ግዕዝ ቋንቋ የካም ዘር የሴም ዘር ቋንቋ መባሉ ቀርቶ በአፍሮ እስያነት እናት ቋንቋ ስር ይጠቃለላል፡፡በዚህ በሶስተኛው ሀሳብ የሚስማሙበት የስነ ልሳን ምሁር የሆኑት ባየ ይማም፣ ደሴ ቀለብ፣ ዮሴፍ ግሪንበርግ እና ሌሎችም የስነ ልሳን ምሁራን ናቸው፡፡ይህን የስነ ልሳን ጥናት መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን አከፋፈል እንመለከት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ከሁለት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰቦች የሚመደቡ ሲሆን እነዚህም አፍሮ እስያነትና ናይሎ ሰሀራ ናቸው፡፡ አብዛኛው የኢትዮጵያ ቋንቋ የሚገኘው በአፍሮ እስያነት እናት ቤተሰብ ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በናይሎ ሰሀራ እናት ቤተሰብ ውስጥ ኮሞን እና ቻርናይል ብቻ በኢትዮጵያ ይነገራሉ፡፡ግዕዝ በአፍሮ እስያነት እናት ቋንቋ ስር ስለሚካተት የዚህን ቋንቋ ቤተሰብ ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡



አፍሮ እስያነት
ኩሽቲክ
ኦሞቲክ
ሴሜቲክ
ደቡብ ሴሜቲክ
ሰሜን ሴሜቲክ
ኢትዮ ሴማዊ
ማዕከላዊ ሴሜቲክ
ሰሜን ኢትዮ ሴማዊ
ደቡብ ኢትዮ ሴማዊ
❖ ግዕዝ
❖ ትግረ
❖ ትግርኛ
❖ አማርኛ
❖ ጉራጌኛ
❖ አደረኛ
❖ ሀረሪ

ከላይ በግራፉ ለማየት እንደሞከረነው አሁን ባለው የስነ ልሳን ጥናት መሰረት  አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚካተቱት በአፍሮ እስያነት እናት ቋንቋ ስር ሲሆን  የግዕዝ ቋንቋ ደግሞ በአፍሮ እስያነት እናት ቋንቋና በሰሜን ኢትዮ ሴማዊ ንዑስ ዘርፍ ስር እናገኘዋለን፡፡

## ፩.፬. የግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ ጥናት (Ethiopian study) ያለው ሚና

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ የሆነው ግዕዝ ከ፫ ሺህ ዘመን በላይ ያስቆጠረ የጽሑፍ ቅርስ የያዘ ቋንቋ ከመሆኑም በላይ በዘመነ አክሱም ብሔራዊ ቋንቋና ዓለም አቀፋዊ ይዘት የነበረው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ኢትዮጵያን በዓለም የጥንታዊ ቋንቋና ስነጽሑፍ ጥናት መድረክ ያስተዋወቀ ቋንቋም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑም ያልዳሰሰው የእውቀት ዘርፍ የለም፡- መንፈሳዊ ድርሳናት ተደርሰውበታል፣ የባህል መድኃኒት፣ የሀገርና የህዝብ ታሪኮች፣ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የፍልስፍና መጻሕፍት ተጽፈውበታል፡፡ ምንም እንኳን ከ፲፱ኛው መ/ክ/ዘ አንስቶ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋነት ሥፍራውን አማርኛ የተረከበው ቢሆንም አሁንም ድረስ በተወሰነ መልኩ ቋንቋው የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው፡፡

ምዕራባውያን የግዕዝ ቋንቋ ከያዘው መረጃ ተጠቃሚ ለመሆን ለበርካታ ዓመታት በቋንቋው ላይ ጥናት ከማከናወናቸውም ባሻገር፣ ለግዕዝ ቋንቋ ጥናት እራሳቸውን የቻሉ የጥናት ማዕከሎች ከፍተው በመስራት ላይ ናቸው፡፡ በሀገራችን ግን በጣት ከሚቆጠሩት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በቀር በግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ላይ የሚደረገው ጥናት ገና አልተስፋፋም፡፡

ስለኢትዮጵያ ሕይወት ልምድ፣ ስለ ባህል የሚፈስ ዕውቀት ትርጉም የሚኖረው በራስ ቋንቋ በሚገኝ ዕውቀት እንጂ ከውጪ የተጻፈን ዕውቀት በመቀበል ብቻ አይደለም፡፡ የግዕዝ ቋንቋ በውስጡ ጠቅልሎ የያዛቸው ብዙ ዕውቀቶች፣ልምዶች፣ፍልስፍናዎችና ታሪኮች አሉ፡፡ የአንድን ሕዝብ ታሪክ፣ ሥልጣኔ ፍልስፋናም መረዳት የሚቻለው በቋንቋውና በሥነ ጽሑፍ ቅርሱ ነው፡፡ ስለዚህ ግዕዝ ቋንቋን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናት ታሪክን ለማገናኘትም ዓይነተኛ ድልድይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ዙሪያ የምትታወቅባቸው ብዙ ቅርሶች አሏት፡፡ከነዚህም ብዙዎቹ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የብራና መጻሕፍት ከነሐረጎቻቸው፣ሥዕሎች፣መስቀሎች፣እንዲሁም ልዩ ልዩ ባህሎች ወዘተ. ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ክርስትናን በይፋ በሃይማኖትነት በ፬ኛው ምዕት

ዓመት በመቀበል ሁለተኛዋ ሀገር በመሆኗ ቅድመ ክርስትናም የእምነተ አይሁድ ሥርዓትን በመከተሏ ያካበተችውን ጥንታዊ የአይሁድና ክርስትና ሥርዓትና ትውፊቶች እንዲሁም የህዝቦች ልዩ ልዩ ባህሎች በጥንታውያን ብራናዎች በብቸኝነት ተጠብቀው የሚገኙት በዚሁ ትውፊት ውስጥ ነው፡፡ በሀገራችን ብዙ ጦርነቶችና ወረራዎች ተደርገው ብዙ ቅርሶቻችን ወድመዋል፡፡ነገር ግን አባቶች ከእሳትና ከወረራ እየደበቁ ያስቀሯቸው ቅርሶቻችን ጥቂቶች አልነበሩም፡፡

በኢትዮጵያ ጥናት የግዕዝን ቋንቋን ጠቀሜታ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል ከእነዚህ መካከል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ ጀርመናዊው ኦገስት ዲልማን የኢትዮጵያን ታሪክ ለመጥናት አንደኛ ግዕዝ ቋንቋ ማወቅ ሁለተኛ ግዕዝ ቋንቋ ማወቅ ሶስተኛ ግዕዝ ቋንቋ ማወቅ በማለት አጽንኦት ሰጥቶታል፡፡

ኢትዮጵያዊው ጌታቸው ኃይሌም (፳፻፰፡፱) ‹‹የዛሬውን ኢትዮጵያዊ ትውልድ ከታሪኩና ከሀገሪቱ የጥንቱ ስልጣኔ ጋር የሚያይዘው በግዕዝ ቋንቋ ቦይነት ከጥንቱ ዓለማችን እየተንዶለዶለ የመጣልን ቅርስ ነው፡፡ኢትዮጵያንም ከጥንት ሀገሮች አንዷ ያደረጋት የመጽሐፍ ባህሏ ነው፡፡ይህ ባህል ከሌላው ሀገር ባህል ጋርም አገናኝቷታል፡፡ከራሷ በመነጨው ስልጣኔ ላይ የሌላ ሀገሮች ስልጣኔ እየቀዳች ያመጣችው በግዕዝ ቋንቋ ነው የኢትዮጵያን የጥንት ታሪክ ብዙ ደራሲዎች ጽፈውልናል ምንጫቸው በአብልጫው የግዕዝ መጻሕፍት ናቸው›› ይላሉ

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ ጥናት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው በመሆኑም በዘመናዊ ትምህርት የግዕዝ መዛግብት የሚኖራቸውን ሚና በዝርዝር እንመለከት፡፡

- በታሪክ ምርምር የኢትዮጵያን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ ወዘተ ታሪክን ለማጠናት የታሪክ መዛግብቱ (ዜና መዋዕላት፣የነገሥታት ደብዳቤዎች፣ ታሪከ ነገሥት፣ ክብረ ነገሥት ወዘተ.) በግዕዝ ከመጻፋቸው አንፃር ቋንቋው መረጃ በማቀበል ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- በስነሰብእ ጥናትና ምርምር፣ በሳይንሳዊ ዘዴ ቋንቋውን ለማጥናት፣ ስለ ቋንቋው ጥንተ ነገርም ሆነ በኢትዮጵያ ለሚደርግ የሥነ-ሰብእ ጥናት የግዕዝ ቋንቋ ጥናት አስፈላጊ ነው፡፡
- የግዕዝ ቋንቋ እጅግ የሚያስደንቅ ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ ያላቸው የጽሑፍ ይትበሀሎች የተመረቱበት ነው፡፡ በግጥም፣ በወጋዊጽሑፍ፣ በህይወት ታሪክ፡ በልብወለድ፣ ወዘተ. የሥነ ጽሑፍ ጥናት ለማድረግ ይረዳል፡፡

- ለህክምና ሳይንስ፣ ለእርሻ፣ ለማእድናት ጥናት ወዘተ. በተለይም የመድኃኒት አይነቶችን (እጽዋትና እንስሳት) በቀላሉ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡
- በብራና መጻሕፍት ላይ ጥናትና ምርምር ለማድረግ፣ የድጂታዜሽን ስራ ለመስራት እና በቤተ መጻሕፍት ለማስቀመጥ፣ ያሉንን ታሪካዊና መንፈሳዊ ቅርሶች ብዛት፣ ዓይነትና ሥርጭት ለማወቅ ይረዳል፣
- በትምህርት መስክ ለቋንቋ፣ ለባህል፣ ለአርኪኦሎጅ፣ለፍልስፍና፣ለታሪክ፣ለፊሎሎጂ፣ ለሥነ-ልሳንወዘተ. አጥኝዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

በአጠቃላይ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ ጉዳዮች በሙሉ የማይነኩት የትምህርት አይነት ስለሌለ ግዕዝ ቋንቋን ማወቅ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ለማወቅ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡

፩.፫. የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ

ኢትዮጵያ ከጥንት ጥቂት ስልጡን ሀገሮች አንዷ ያደረጋት የመጽሐፍ ባህሏ ነው ብለናል፡፡ይህን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ ለምሳሌ Addisie (2009,1) Ethiopia is one of the oldest countries with rich culture and civilization. Literatures which are written about ancient civilization confirm that the country is one of the few countries which have their own writing culture.The country passes through monumental and manuscript writing system starting from 1st millennium BCE.This writing tradition is still practiced in limited significance.

Sergew (1972,1) also substantiate this truth the people, they live around Mediterranean sea, Red sea and the rivers Tigris and Euphrates were the first civilized people and they recorded history. Thus Ethiopia included with this countries they developed ancient time, because Ethiopia located around Red sea and the great river, the Blue Nile.

According to Bausi, Ethiopia is, “Historically a land of written civilizations since the beginning of the 1st millennium BCE …the areas now a days corresponding to the highlands of Eritrea and Northern Ethiopia witnessed the early introduction of the parchment roll and codex, the latter

having been strongly fostered by the Christianization of the country in the 4th century CE.” In addition to this, Taddesse (1972, 23-25) stated that the coming of nine saints from Syria in the end of 5th century was important period for the Ethiopian literature to be flourished because the time was the turning point of writing and translating religious books via Ethiopic (Geez) language.

Written manuscripts available today are translated, adopted and indigenous works. According to Bausi (2015, 158-59), Ethiopic manuscripts are classified into three formats: the roll (scroll) and the rotulus (*kətab, ṭälsäm*), the miscellaneous forms (*sənsul*) andthe codex (*mäṣḥaf*).

ከላይ እንዳየነው ኢትዮጵያ ቅ.ል.ክ ፩ኛው ሚሊኒየም መጀመሪያ አንስቶ የጽሑፍ ባህል እንደነበራት በብዙ ምሁራን ተገልጿል፡፡ የተጻፈበትን ጥሬ እቃ ስንመለከት በቅደም ተከተል ቀንድ፣ድንጋይ፣ሳንቲም፣ ብራና ወዘተ. ሲሆኑ እንዲሁም ከ ፲፱ኛው ክ/ዘመን ወዲህ ደግሞ ቴክኖሎጅ በመስፋፋቱ የመጽሐፊያ ጥሬ እቃው ወረቀት ሆኖ እናገኛዋለን ፡፡ እነዚህን የመጽሐፊያ ጥሬ እቃዎች በሁለት ሸካራና ለስላሳ ብለን መክፈልም እንችላለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የግዕዝን ስነጽሑፍ በዘመን ፩. የአክሱም ዘመን ከ፫ኛው እስከ ፯ኛውክ/ዘመን ያለውን ዘመን ሲያጠቃልል በዚህ ዘመን የግዕዝ ስነጽሑፍ በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋበት ነበር ምክንያቱም ነገሥታቱ ለምሳሌ ኢዛና ታሪካቸውን በድንጋይ እና ሳንቲሞቸ ላይ ማጻፋቸው ፣ ቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰለማ ከሳቴ ብርሃን) የመጀመሪያው የአክሱም ጳጳስ ሆነው መሾማቸውና ከ335-400ዓ.ም ባለው በግዕዝ ቋንቋ ለውጥና እድገት ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው፣ ተሰዓቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን በ፭ኛውና በ፮ኛው ክ/ዘመን ከመካከለኛው ምስራቅ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውና የተለያዩ መጽሐፍትን ከተለየዩ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ መተርጎማቸው ምሳሌ አቡነ አረጋዊ፣አባ ጴንጤሊዎን፣ አባ የማዓታ፣አባ ገሪማ ወዘተ. ብሉይና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሱርስት፣ አርባዕቱ ወንጌሎች

ከግሪክ፣መጽሐፈ ሰርዓተ መነኮሳት ከግብጽ ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል እንዲሁም ገዳማዊ ህይወትን በማስፋፋት ለተለያዩ ሀገር በቀል ስነጽሑፎች ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው፣ ሌሎች የአክሱም ነገሥታትም ከ፬-፰ኛው ክ/ዘመን ግዕዝን ብሄራዊ ቋንቋ ማድረጋቸው፣ በ፮ኛው ክ/ዘመን የቅዱስ ያሬድ መነሳትና ድርሰት በግዕዝ ማበርከቱ (ምሳሌ መዝገበ ድጓ፣ አንቀጸ ብርሃን) እነዚህ በሙሉ ለግዕዝ ሥነጽሑፍ በአክሱም ዘመን ማደግ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡፪. የጨለማው ዘመን ከ፱ኛው እስከ ፲፪ኛው ክ/ዘመን ያለው ሲሆን የጨለማ ዘመን የተባለበትም ምክንያት በዮዲት ጉዲት መነሳት እንዲሁም በሰሎሞናዊ ስርዎ መንግሥትና በዛጉዌ ስርዎ መንግሥት መካከል በነበረው ሽኩቻ ምክንያት በፊት የነበሩ ብዙ የስነጽሑፍ ሀብቶች መውደማቸው እንዲሁም የግዕዝ ስነጽሑፍ ባህል መዳከምና ቀጣይነት አለመኖር ነው፡፡፫ኛው የወርቃማው ዘመን ሲሆን ይህም ከ ፲፫ ኛው ክ/ዘመን እስከ ፲፰ ኛው ክ/ዘመን ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ዘመን የግዕዝ ስነጽሑፍ በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶ ነበር ምክንያቱ ደግሞ ባለፈው ዘመን እንቅፋት ሆኖ የነበረው የስልጣን ሽኩቻ በ፲፪፻፸ ዓ.ም ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማብቃቱ፣ የሚርትና ጥንቆላ እምነት በመስፋፋቱ (ምክንያቱም ጥንቆላው የሚካሄደው በጽሑፍና ክታብን ለህብረተሰቡ በመስጠት ስለሆነ፣ ለነዚህ ጸሐፍት መልስ የሚሆኑ የሃይማኖት መጻሕፍትን የሃይማኖት ሊቃውንቶች መጻፋቸው ለዚህም እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱት ሰዎች ንጉሡ ዘርዐ ያቆብና (መጽሐፈ ብርሃን፣መጽሐፈ ሚስጢር፣ታዕቅቦ ሚስጢር፣ክህደተ ሰይጣን ወዘተ.) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ(አርጋኖን፣ውዳሴ ሀዋርያት፣ውዳሴ መስቀል፣ቅዳሴያት፣ኖህተ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምስጢር፣ፍካሬ ሃይመኖት ወዘተ.) ናቸው፡፡ ሌላው ሀገር በቀል የሆኑ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች ክብረ ነገሥትን ጨምሮ በሊቃውንት መጻፋቸው ነው፡፡

፬ኛው ከ፲፮ኛው-፲፱ኛው ክ/ዘመን ያለውን ጊዜ የሚይዝ ነው፡፡የግዕዝ ስነጽሑፍ በዘመናት የነበረውን ታሪክ ስንመለከት ዚግዛግ የሚሰራ ዓይነት ሆኖ እናገኛዋለን፡፡ ከዚህ በፊት

እንደተመለከትነው በዘመነ አክሱም የግዕዝ ስነጽሑፍ በነሥታቱም፣ በሃይማኖት መሪዎች (በተሰዓቱ ቅዱሳን፣ ቅዱስ ያሬድ አባ ሰላማና ሌሎች)ምክንያት አብቦ ነበር፡፡ በኋላ ግን በሰሎሞናዊ የአክሱም ነገሥታት እና በዛጉዌ ነገሥታት አለመግባባት እንዲሁም በዮዲት ጉዲት መነሳት ምክንያት በግዕዝ የመጽሐፍ ባህሉ ተዳክሞ ነበር ከዚህ አልፎም ባለፉው የአክሱም ዘመን የተጻፉት ብራናዎች ወድመዋል፡፡ ለዚህም ነው ከ ፱-፲፪ ክ/ዘመን ያለው ጊዜ የግዕዝ ስነጽሑፍ የጨለማ ዘመን የተባለው፡፡ከዚያም ዮዲት ጉዲት ስትወድቅና የሰሎሞናዊ ስርዎ መንግሥት እንደገና ሲያንሰራራ የግዕዝ ስነጽሑፍም እንደገና አንሰራርቷል፡፡ ከዚያ ዘመን በኋላ ደግሞ በግራኝ አህመድ ዘመን ብዙ ቅርሶች ብራናዎችን ጨምሮ በመውደማቸው በተጨማሪም በአጼ ሱስንዮስ ዘመን የካቶሎክ ሃይማኖት የሀገሪቱ ሃይማኖት ሆኖ በመታወጁ ምክንያት በሁለቱም ማለትም በኦርቶዶክስና በካቶሎክ ሃይማኖት መካከል በተነሳው ጦርነት ምክንያት የግዕዝ ብራናዎች ወድመዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ በጎንደር ዘመን የግዕዝ ስነጽሑፍ እንደገና ያበበበት ዘመን ነበር፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የጎንደር ነገሥታት ምሳሌ አድያም ሰገድ እያሱ፩ ለቁም ጸሐፊዎች ርስት በመስጠት፣ ብራና የሚጸፍባቸው ራሳቸውን የቻሉ ህንጻዎችን በማስገንባታቸው፣ የፈላስፋው ዘርዓያቆብ መነሳት፣ በዘመኑ የነበረው የጸጋ፣የቅባት እንዲሁም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መከራከሪያ ቋንቋ መሆኑ የግዕዝ ስነጽሑፍ እንደገና ያበበት ዘመን አስብሎታል፡፡

ከዚያ በኋላ ደግሞ በዘመነ መሳፍንት እርስ በርስ በነበረው ሽኩቻና አጼ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕላቸውን ሳይቀር በአማርኛ በማጻፋቸው የግዕዝ ስነጽሑፍ እየተዳከመ መጥቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የግዕዝ ስነጽሑፍ እየተዳከመ በዘመናችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ሆኖ እናገኛዋለን፡፡ የስነልሳን ምሁራን አንድ ቋንቋ አፉን የሚፈታበት ትውልድ ከሌለ የሞተ ነው ቢሉም ግዕዝ ቋንቋ ግን በአንድ ተቋም የተወሰነ ይሁን እንጅ ተናጋሪ ያለውና ጥንት በነበሩት ዛሬም በአሉት የግዕዝ ስነጽሑፍ መጻፊያ

ቦታዎች አሁን ድረስ የሚጻፍበት ቋንቋ ነው፡፡ ከእነዚህም ዋና ዋናዎቹ ተጉለት፣ ተንቤን፣ ጉንዳጉንዴና እና አንዳቤት ናቸው፡፡

### ፩.፫.፩. የግዕዝ ስነጽሑፍ ሀብቶች ዝርዝር

የግዕዝ ስነጽሑፍ ሀብቶችን ከምንጭ አንጻር በአጠቃላይ በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን ከውጭ የተተረጎሙ (Translated works)፣ በውጭ አጻጻፍ ስታይል የተጻፉ (Adopt works)፣ ሀገር በቀል ስራዎች(indigenous works) ናቸው፡፡የተጻፉበት ቋንቋም ግዕዝ ብቻ አልነበረም በተለይ ጥንታዊዎቹ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በግሪክ፣ በሳባ (ደቡብ ዓረቢ) ርባታ በሌለው ግዕዝና ርባታ ባለው ግዕዝ የተጻፉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡የሀገራችን ኢትዮጵያ የጽሑፍ ታሪክ የሚጀምረው ፩ኛው ሚሊኔም ጀምሮ መሆኑን አብዛኛዎቹ የግዕዝ ስነጽሑፍ ምሁራን የሚሳማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ሀገራችን ያላት የስነጽሑፍ ሀብት በበቂ ሁኔታ ያልተጠና ከመሆኑ የተነሳ በትክክል የተጠኑ (የታወቁ) የግዕዝ ስነጽሑፍ ሀብቶች ዝርዝር የምናገኘው ግን ከድንጋይ ላይ ጽሑፍ ዘመን ጀምሮ ነው፡፡እነዚህ ሀብቶች ከላይ እንዳየነው በድንጋይ፣በእንጨት በቀንድ፣ በሳንቲም፣ በብራና እንዲሁም በወረቀት ጥሬ እቃዎች የተጻፉ ናቸው በዚህ መሰረት ከተጻፉበት ቁሳቁስ አንጻር ሽከራና ለስላሳ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

**የአክሱም ዘመን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች**

የአክሱም ዘመን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ከቋንቋ አንጻር በግሪክ፣ በሳባ፣ርባታ በሌለው ግዕዝ እና ርባታ ባለው ግዕዝ የተጻፉ ናቸው፡፡ ከይዘት አንጻር ደግሞ ስለ ዘመኑ ነገሥታት እምነትና ታሪክ የያዙ ናቸው፡፡

የአክሱም ዘመን የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ተብለው የሚታወቁት በኢትዮጵያና በጎረቤት ሀገራት ይኸውም በደቡብ ዐረቢያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳን እንዲሁም በኢትዮጵያ (አክሱም፣ የሃ፣

መተራ፣ ጴንጤሊዎን፣ ደብረ ዳሞ፣ እንደጭርቆስ ወዘተ.)የተገኙ ሲሆን ቁጥራቸው ከ100 የበለጡ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች በምሁራኑ ተገኝተዋል፡፡

በተለይ ደግሞ በጀርመኑ ኢኖ ሊትማን (Enno Littman in 1906) የተመራው ቡድን በአክሱም የድንጋይ ላይ ጽሑፎች ላይ አራት ቅጽ (volume) ያለውን Deutsche Aksum Expedition (DAE) የተሰኘውን ስራ አበርክቷል፡፡ሊትማን የድንጋይ ላይ ጽሑፎቹ በቁፋሮ ከተገኙ በኋላ የተገኙበትን ቦታና የአጻጻፍ ዘመናቸውን መሰረት በማድረግ በቁጥር ተራ ቅደም ተከተል አስቀጧቸዋል፡፡ እነዚህም

፩. አባ ጴንጤሊዎን 1 በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን አንድ ስሙ ያልታወቀ ንጉሥ ጦርነት ማሸነፉን ይገልጻል፡፡

፪. አባ ጴንጤሊዎን 2 በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን አንድ ስሙ ያልታወቀ ንጉሥ ጦርነት ማሸነፉን ይገልጻል፡፡

፫. አባ ጴንጤሊዎን 3 አንድ ስሙ ያልተገለጸ ንጉሥ የእምነት ቦታ መጎብኘቱን ይገልጻል፡፡

፬. አክሱም 4 በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ንጉሥ ኢዛና ጦርነት ማሸነፉን የሚገልጽ ነው፡፡

፭.አክሱም 5 ከአክሱም 4 ቀጥሎ የተቀመጠ ከመሆኑ ባሻገር ድንጋዩ ስለተሰበረ የያዘውን መልዕክት ማወቅ አልተቻለም፡፡

፮. አክሱም 6 በሳባ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ይዘቱ ሀውልትን መንከባከብ እንደሚገባና የማይንከባከብና የማይጠብቅ ቅጣት እንደሚደርስበት የሚገልጽ ነው፡፡

፯. አክሱም 7 ርባታ በሌለው ግዕዝ ቋንቋ በግዕዙ ፊደል ብቻ የተጻፈ ሲሆን በይዘቱ ንጉሥ ኢዛና ጠንካራ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

፰.አክሱም 8 በሳባ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ንጉሥ ኢዛና ለአምላኩ ለመሐረብ ምስጋና ማቅረቡን ያስረዳል፡፡

፱.አክሱም 9 ርባታ ባለው ግዕዝ የተጻፈ ሲሆን ይዘቱ ስለኢዛና ጥንካሬ ይገልጻል፡፡

፲ አክሱም 10 ርባታ ባለው ግዕዝ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ፊደላቱ በዚህ ዘመን ከግዕዝናዊነት ወደ ኅባባነት የተለወጡበት ዘመን ነው፡፡ ይዘቱ ደግሞ ኢዛና ጦርነት መግጠሙን ያሳረዳል፡፡

፲፩. አክሱም 11 በቋንቋም ሆነ በይዘት ከአክሱም 10 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

፲፪. አክሱም 12 በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ ብሎ ስለሚጀምር ክርስትና የሀገሪቱ ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑን ወይም ኢዛና ንጉሠ አክሱም ክርስትናን በይፋ መቀበሉን ያመለክታል፡፡ከድንጋይ ላይ ጽሑፍ በተጨማሪ የሳንቲም ጽሑፎችንም በኢዛና ዘመን እናገኛለን፡፡ከድንጋይ ላይ ጽሑፍ ቀጥሎ በ5ኛው ክፍለ ዘመን ተሰዓቱ(9ኙ) ቅዱሳን ከመካከለኛው ምስራቅ በተለይ ከሶሪያ በመምጣት ቁርሎስ፣አራቱ ወንጌሎች፣ ፊሳልጎስ፣መጽሐፈ ስርዓተ መነኮሳት ወዘተ ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል፡፡በተለይ ደግሞ በ6ኛውና በ7ኛው ክ/ዘመን እንደተጻፈ የሚነገርለት የአባ ገሪማ ወንጌል የጽሑፍና የሀረጋት ውበቱ የተለየና የመዛግበት ተማራማሪዎችን ያስደመመ ነው፡፡በዚሁ ዘመን የተነሳው የቅዱስ ያሬድ ስራዎችም ተጠቃሾች ናቸው፡፡በግዕዝ ስነጽሑፍ የጨለማው ዘመን እየተባለ በሚጠራው በዛጉዌ ዘመን ደግሞ ክብረ ነገሥት ከአረብኛ ወደ ግዕዝ ተተርጉሟል፡፡ከ13ኛው ክ/ዘመን በኋላ ደግሞ ለግዕዝ ስነጽሑፍ ወርቃማ ዘመን ስለነበረ ብዙ ብራናዎች ተጽፈዋል፡፡ እንዲያውም በዘመናችን ያሉት አብዛኛዎቹ ብራናዎች በመካከለኛው ዘመን የተጻፉ ናቸው፡፡በአጠቃላይ አማርኛ ቋንቋ የስነጽሑፍ ቦታውን እስከተረከበበት እስከ 19ኛው ክ/ዘመን ድረስ በግዕዝ የተጻፉ ብራናዎች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ ቁጥራቸውን በትክክል ለማወቅ አይቻልም፡፡ይሁን እንጅ በግዕዝ ስነጽሑፍ ሀብት ምርምር ያደረጉት ስርግው ሐብለስላሴ 1981 በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች ያሉ መጻሕፍት ክታብን ሳይጨምር ከ200,000

እንደሚበለጥ ግምታቸውን ሲያስቀምጡ በውጭ ሀገር የሚገኙ ብራናዎችም ቁጥራቸው ከሀገር ውስጥ እንደሚስተካከል ያብራራሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ስለ ብራና ጽሑፍ ብዛት ያጠናው አምሳሉ ተፈራ በኢትዮጵያ ከ1,500,000 በላይ ብራናዎች እንደሚገኙ ይገልጻል፡፡ በሀገራችን መዘርዝር (ካታሎግ) የተሰራላቸውና ጥናት የተደረገባቸው የብራና መጻሕፍት ተቋማት የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀገር ውስጥ ጎይቅ እስጢፋኖስ 200፣ ጉንዳጉንዶ 800፣ደብረ ቢዘን 572፣አክሱም 100፣ IES 1500፣ NALA 850 ናቸው፡፡

ከሀገር ውጭ ደግሞ Vatican 1082, France 1000, British 624, Birlin 328, Minesota USA 9238 Micro Film ሲገኙ እነዚህም በስጦታ፣ በግዥ እና በዘረፋ የወጡ ናቸው፡፡ በግለሰብ ደረጃ ጀምስ ብሩስ ዲአባዲ እና ካውሌይ ብዙ መጻሕፍትን ወደ ውጭ አግዘዋል፡፡

የዚህን ሁሉ የብራና መጻሕፍት አጠቃላይ ይዘቱን በሁለት ዓለማዊና መንፈሳዊ በማለት መክፈል ይቻላል፡፡በዝርዝር ለማየት ያክል፡-

**የሃይማኖት መጻሕፈት**

| የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች | ሥነ መለኮት |
|---|---|
| ✓ ገድላት | የዶግማ መጻሕፍት |
| ✓ ቅዳሴያት | የቀኖና መጻሕፍት |
| ✓ የገዳማት ስርዓት | የመድኃኒት መጻሕፍት |
| ✓ የዜማ መጻሕፍት | መጽሐፈ መድኃኒት |
| ✓ ድርሳናት | መጽሐፈ ፈውስ |
| ✓ የጸሎት መጻሕፍት | እጸ ደብዳቤ |
| | መጽሐፈ ማይ |
| | ክታብ፣ መጽሐፈ አእባን ወዘተ. |

ታሪክ

- ✓ ዜና መዋዕላት
- ✓ ክብረ ነገሥት
- ✓ ታሪከ ነገሥት
- ✓ የነገሥታት ደብዳቤዎች
- ✓ የነገስታት የሳንቲምና የድንጋይ ላይ ጽሑፎች

ስነፌለግ

- ✓ አውደ ነገሥት
- ✓ አቡሻኽር
- ✓ መጽሐፈ ሄኖክ
- ✓ መጽሐፈ ንድቀት

ፍልስፍና

- ✓ ሀተታ ዘዘርዓ ያቆብ
- ✓ ወልደ ህይወት
- ✓ አንጋሪ ፈላስፋ
- ✓ ፊሳልጎስ
- ✓ መጽሐፈ ፍልስፍና ወዘተ.

ግብርና

መጽሐፈ ገራህት

በአጠቃላይ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉና በሀገር ውስጥና ውጭ ሀገር የሚገኙ ብራናዎች በቁጥር በጣም ብዙ ሲሆን በይዘትም የማይነኩት የዕውቀት ዘርፍ የለም ስለዚህ እነዚህን ብራናዎች መመርመር ለሀገረም ሆነ ለዕውቀት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

### ፩.፫.፪. የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት

በዓለም ላይ የራሳቸው ፊደል ካላቸው ጥቂት ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ ናት፡፡ ይኸውም የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት ሲሆኑ እነዚህ ፊደላት ለሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎችም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ስለ ፊደላት ጥንተ አመጣጥ የቋንቋ ምሁራን የተለያዩ መላምቶችን ያስቀምጣሉ ለምሳሌ ኪዳነ ወልድ ክፍሌና ለይኩን ብርሃኑ የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት የተገኙት ከእግዚአብሔር ሲሆን እግዚአብሔር ሄኖስን እንደ ሙሴ ስቦ (ጠርቶ) ህግና ስርዓትን አጉልተው የሚያሳዩ ፳፪ ፊደላትን በጸፍጸፈ ሰማይ (በሰማይ ሰሌዳ)  በ፳፪ቱ ስነ ፍጥረታት ምሳሌ አድርጎ ሰጠው በማለት ያስረዳሉ፡፡ስለዚህ እንደነዚህ ምሁራን እምነት ፊደላት የተገኙት በሄኖስ አማካኝነት ከፈጣሪ ነው፡፡ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ፊደላት የሰው ልጅ ድምጽ ውክልና፣ ፎቶ ግራፍ ናቸው ስለዚህ ፊደላት የተፈጠሩት በሰውልጆች ስምምነት ነው ይላሉ፡፡ ከዚሁ ሀሳብ ጋር የተያያዘ የስነ ልሳን ተመራማሪዎችም ፊደልን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለሰፉ ሱመራዊያን (የሰው ልጆች) ሲሆኑ እነዚህም ብዙዎቹ አሁን ኢራን በሚባለው አካባቢና ከፊሎቹ ደግሞ በግብጽና በሜሶፐታሚያ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ፊደላትም ከደቡብ አረቢያ ባህር ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ኢትዮ ሴማዊያን አማካኝነት ከ3000 ዓመታት በፊት  በኢትዮጵያ አገልግሎት ላይ ውለዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንደ ጌታቸው ኃይሌ ገለጻ ደግሞ ‹‹ሴማዊያን ቋንቋዎች ከአንድ የመነጩ የሚመስሉ፣ የሚመሳሰሉና ተመሳሳይነታቸውን የቀነሱ የየራሳቸው ፊደላት አላቸው፡፡ለምሳሌ ግዕዝና ደቡብ ዐረቢ በመጠኑ ይመሳሰላሉ፡፡ምክንያቱ ከሁለት አንዱ ሊሆን ይችላል ግዕዝ ከሳባ ወይ ሳባ ከግዕዝ ወይ ደግሞ ሁለቱም ከአንድ ምንጭ ቀድተዋል፡፡ እውነቱ የቱ እንደሆነ ለጊዜው ማስረጃ ስሌለለን ግዕዝ ከሳባዊያን ወይም ሳባዊያን ከግዕዝ ወስደዋል ማለት ስህተት ነው፡፡ተመሳሳይነት ለዝምድና እንጅ አንዱ ከሌላው ለመቅዳቱ ማስረጃ አይሆንምና፡፡በርግጥ የሳባ ፊደል ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኝቷል የተገኘው ግን የሳባ ቋንቋ

ተጽፎበት ነው፡፡ ግዕዝም በራሱ ፊደል እንጅ በሳባ ፊደል ተጽፎ አያውቅም፡፡ግዕዝ የራሱ ፳፮ ፊደላት አሉት፡፡ከላይ ካየነው የጌታቸው ኃይሌ ሀሳብ በተለየ ሀላሽና ግላሰሪ የተባሉ ተመራማሪዎች ከድንጋይ ላይ ያገኟቸውን የሳባ ጽሑፎች መሰረት በማድረግ ሳባ ፳፱ ፊደላት አሉት ከእነዚህ ውስጥ ግዕዝ ፳፬ ወስዶ የራሱን ሁለት ፊደላት (ፐ እና ጰ) ጨምሮ ፊደላቱን ፳፮ አድርጓል ይላሉ፡፡እነደነዚህ ምሁራን ገለጻ ለውጡ የፊደላት ብቻ ሳይሆን የአቅጣጫ፤ የፊደል ገበታ ከ አ፣በ፣ገ፣ደ ወደ ሀ፣ለ፣ሐ፣መ ፤ከአናባቢ አልባነት ወደ አናባቢነት ጭምር ነው፡፡ከፊደል ገበታ ጋር ተያይዞ ያለውን ሀሳብ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌም ይጋሩታል፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ከላይ እንዳየነው ፳፪ ቱን አሌፋት ፈጣሪ ለሄኖስ ሰጠው ካሉ በኋላ ሁሉም የሴም ቋንቋዎች የፊደል ገበታ አ፣በ፣ገ፣ደ ነበር ግዕዝም በኋላ ተለውጦ ነው እንጅ የፊደል ገበታው አ፣በ.ገ፣ደ ነበር በማለት ‹‹ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃለት ሐዲስ የሚለውን መጻፋቸውን ያዘጋጁት በዚሁ በአ፣በ፣ገ፣ደ ፊደል ተራ ቅደም ተከተል ነው፡፡ ጌታቸው ኃይሌ ደግሞ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመሰላቸው ሄዱ እንጅ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ግዕዝ የራሱን ነው የተከተለ የሚለውን ሀሳብ ያጠነክራሉ፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆን ሌሎች ቋንቋዎች

አ  አልፋ/አሌፍ

በ  ቤት/ቤታ

ገ  ጋሜል እያሉ ሲደረድሩ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ

ሀ  ሆይ

ለ  ላሜድ/ላምዳ

ሐ  ሐመር

መ  ማይ እያሉ መደርደራቸው የፊደል ገበታ ልዩነታቸው ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ማስረጃ ነው ይላሉ፡፡ በአጠቃላይ ግን የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት መገኛና ከሌሎች ሴማዊ

ቋንቋዎች ጋር ያላቸው ዝምድናና ልዩነት አከራካሪ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያይዞ የሴም ቋንቋ ፊደላት የፊደል ገበታ ልዩነት አላቸው ሲባል ፊደላቱ ተመሳሳይነት የላቸውም ለማለት እንዳልሆነ ልንገነዘብ ያስፈልጋል፡፡ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የሴሜቲክ ቋንቋዎች ተመመሳይ ፊደላት አላቸው፡፡ ፊደላቱ ከአንድ ምንጭ የተነሱ ለመሆናቸው ማስረጃ የሚሆኑ ከየቋንቋው ያሉትን ፊደላት ከዚህ በታች እንመለከታለን፡፡ ለይኩን ብርሃኑ ከገጽ 35-37 ያለውን ይመልከቱ፡፡

እንደ አንዳንድ ምሁራን ገለጻ የላቲን አሌፍ ቤት/Alphabet/ ሳይቀር ከስማቸው እንደመንረዳው የተወሰዱት ከሴሜቲክ ቋንቋዎች ነው፡፡

ሀ. የግዕዝ ፊደላት መሠረታዊ ለውጥ

ከላይ ካየነው ከሀላሽና ግላሰሪ ሀሳብ በተጨማሪ እንደ ዘርዓ ዳዊት ገለጻ ማንኛም ቋንቋ ለውጥ እንደሚያደርገው ሁሉ ግዕዝ ቋንቋም በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በቅዱስ ፍሬሚናጦስ (ሰለማ ከሳቴ ብርሃን) ዘመን ከ335-350 ባሉት 15 ዓመታት ውስጥ መጻሕፍትን ከውጭ ቋንቋ ለመተርጎም በሚያመች መንገድ በግዕዝ ቋንቋ ላይ ለውጥ አድርገውበታል ይላል፡፡ ይኸውም

፩. ከአናባቢ አልባነት ወደ አናባቢነት ኧ፣ ኡ፣ኢ፣ኣ፣ኤ፣እ፣ኦ፤

፪. ፊደላቱ ከግዕዝ (አንደኛ) ፊደል በደ ሳብዕ/ሰባት) ርባታ የተደረገበት፤

፫. የጽሕፈት ስርዓት የአቅጣጫ ለውጥ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ እየተመላለሰ ይጻፍ የነበረው ከግራ ወደ ቀኝ ብቻ እንዲጻፍ አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ግዕዝ እነዚህን ስነልሳናዊ ለውጦች አድርጎ ፳፮ መደበኛ ፊደላትን ይዞ ከዘመናችን ደርሷል፡፡ አማርኛ ደግሞ ከ፳፮ቱ ፊደላት ሰባት ፊደላትን በመጨመሩ መደበኛ ፊደላቱ ፴፫ ሲሆኑ አምስት ዲቃላ ፊደላትን ይጨምርና አጠቃላይ ፊደላቱ ፴፰ ናቸው፡፡

**ለ. የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት ትርጓሜና ጠቀሜታ**

የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት ሃይማኖታዊ ትርጉም፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ አኀዛዊ መግለጫ እንዲሁም ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ፊደላት በቃላት የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው ለይኩን ብርሃኑ፣ የስነልሳን ተመራማሪዎችና የተለያዩ መዛግብት ስረዳሉ፡፡

ሥዕላዊ መግለጫ የግዕዝ ቋንቋ ፊደላት ከተፈጠሮ እንደተቀዱና የፈለሰፏቸው ምሁራንም ተፈጥሮን በመመልከትና ከተፈጥሮ በመቅዳት ፊደላትን እንደፈጠሩ ከላይ የጠቀስናቸው ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

ለምሳሌ

ነ ከእባብ

ዐ ከዐይን

ፈ ከአፍ

ተ ከመስቀል

በ ከቤት

ሰ ከሰው ተቀድተውና ተሥለው እናገኛለን፡፡

**ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ፊደላት በቃላት መካከል የትርጉም ልዩነት፡-** በግዕዝ ቋንቋ አንዳንድ ፊደላት የተለያየ ቅርጽና ተመሳሳይ ድምጽ አላቸው፡፡ለምሳሌ ሶስቱ ሀ፣ሐ.ኀ ዎች ሁለቱ ጸ፣ፀ፤ ሰ፣ሠ ዎች እንዲሁም የአንድ ፊደል ግእዙና ራብዑ (የመጀመሪያውና አራተኛው) ፊደል ሀሃ፣ሐሓ፣ ኀኃ፣ አኣ፣ ዐዓ ተመሳሳይ ድምጽ አላቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት በአሁኑ ወቅት ያሉ የስነልሳን ምሁራን እንደሚሉት አንድ የፊደል ገበታ የሚጋሩት ግዕዝና አማርኛ ለአንድ ድምጽ ከአንድ በላይ የሆኑ ፊደላት አላቸው ይህ ደግሞ ጊዜን ጉልበትንና መዋእለ ንዋይን ያባክናል ይላሉ፡፡ይህን ሀሳብ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚም ተቀበሎት በዚህ ተቋም የሚሰሩ ስራዎች ፊደላትን ቀንሰው

እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ይህ ሀሳብ ምሁራንን ከሁለት ጎራ ከፍሏል ምክንያቱም በተለይ በጥንታዊ ቋንቋ ላይ ምርምር ያደረጉ ምሁራን በዚህ ሀሳብ አይሰማሙም፡፡ከነዚህ ምሁራን አንዱ የሆኑት ጌታቸው ኃይሌ ‹‹ በመሠረቱ በቋንቋና በፊደል ውስጥ ትርፍ ነገር የለም፡፡ አንድ ድምጽ የሚያስፈልገው አንድ ሆሄ ብቻ ነው፡፡ጥቂት ድምጾች ሆሄ ከተቀረጸላቸው በኋላ ጠፉ፡፡ ሆሄዎቻቸው አብረው እንዳይጠፉ በየመጻሕፍቱ አሉ፡፡››ይላሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ሁሉም ፊደላት የየራሳቸው የተለያየ ድምጽ ነበራቸው አሁን ግን ጠፍተውብናል፡፡ ድምጻቸው ቢጠፋም ቅርጻቸው ግን በየመዛግብቱ አለ፡፡ ስለዚህ ፊደላትን እንቀንስ ማለት ድምጻቸውን እንዳጠፋን ሁሉ ቅርጻቸውንም እናጥፋ እንደማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፊደላቱ መቀነስ የሚያስከትለው የተለያዩ ችግሮች አሉ እነዚህም፡፡ከዚህ በፊት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉትን የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የመድኃኒት፣ የሃይማኖት ወዘተ መጻሕፍትን ለመረዳት ስለሚያስቸግር ምክንያቱም ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ፊደላት በቃላት ውስጥ የተለያየ ትርጉም ስላቸው ነው፡፡

ምሳሌ ኀላፊ፡- ጠፊ ሚች

ሐላፊ፡- አለቃ፣ተጠሪ መሪ

ሠረቀ፡- ወጣ

ሰረቀ ፡- የሰው ገንዘብ ወሰደ

አቢይ ፡- እምቢ አለ

ዐቢይ፡- ታላቅ፣ገናና፣ብርቱ

መሓሪ ፡- ይቅር ባይ

መሀሪ ፡- አስተማሪ ወዘተ. እንደዚህ እያልን ብንሄድ አብዛኞዎቹ የግዕዝ ቃላት በፊደል ቅርጽ መለዋወጥ ምክንያት የተለያየ ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ስለዚህ ፊደላትን መቀነስ የመዛግብትን ትርጉም ማዛባት ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዓለም የራሳቸው የጽሕፈት ስርዓትና ፊደል ያላቸው ሀገራት ጥቂት እንደሆኑና ከእነዚህ ጥቂት ሀገራት ውስጥ በግዕዝ የፊደላት ባለቤትና ቀዳሚ ስልጡን ሀገር ኢትዮጵያ ናት ብለናል ይህ ቀደምት ስልጣኔዋም በዓለም የቀዳሚ ቋንቋዎች ጥናት እንድትካተት አድርጓታል ስለዚህ እነዚህን ፊደላት መቀነስ ስልጣኔዋንና የስልጣኔ መገለጪዋን እንደመቀነስና ታሪክ እንደማጥፋት ይቆጠራል፡፡

ሌላው እያንዳንዳቸው ፊደላት ያላቸው ሃይማኖታዊ እንዲሁም አኀዛዊ መገለጫና ቅርጽ ያሳጣል፡፡ ከዚህ አንጻር ፊደላትን ባሉበት ጠብቆ መያዝና ጠንቅቆ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የፊደላትን ሃይማኖታዊና አኀዛዊ መግለጫ ለይኩን ብርሃኑ ከገጽ 17-35 ተመልከቱ፡፡

### ፩.፭.፫. የግዕዝ ቋንቋ አኃዝ

ግዕዝ ቋንቋ አስራ ዘጠኝ መሰረታዊ ድጅት ያለው አኃዝ አለው እነዚህን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | አሐዱ | አንድ |
| ፪ | ክልዔቱ | ሁለት |
| ፫ | ሠለስቱ | ሶስት |
| ፬ | አርባዕቱ | አራት |
| ፭ | ኀምስቱ | አምስት |
| ፮ | ስድስቱ | ስድስት |
| ፯ | ሰብዓቱ | ሰባት |
| ፰ | ስምንቱ | ስምንት |
| ፱ | ተሰዓቱ | ዘጠኝ |
| ፲ | ዐሥርቱ | አስር |

፳ ዕስራ ሃያ

፴ ሠላሳ ሰላሳ

፵ አርብዓ አርባ

፶ ኀምሳ አምሳ

፷ ስድሳ ስሳ ስልሳ

፸ ሰብዓ ሰባ

፹ ሰማንያ ሰማኒያ

፺ ተስዓ ዘጠና

፻ አሐዱ ምእት /ምእት/ አንድ መቶ

፲፻ ዐሥርቱ ምእት አንድ ሺህ

፳፻ ዕሥራ ምእት ሁለት ሺህ

፼ እልፍ አስር ሺህ

፲፼ አእላፍ መቶ ሺህ

፻፼ አእላፋት አንድ ሚሊዮን፣ አእላፈ፣ ትእልፊት እያለ ይቀጥላል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ ፊደላትን 1ኛ 2ኛ እያለን ለመጥራት ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ግዕዝ (አንደኛ)፣ ካዕብ (ሁለተኛ)፣ ሳልስ (ሶስተኛ)፣ ራብዕ (አራተኛ)፣ ኃምስ (አምስተኛ)፣ ሳድስ ( ስድስተኛ)፣ ሳብእ ( ሰባተኛ) ናቸው፡፡

ተማሪዎች ስለ ግዕዝ ፊደልና አኃዝ ለበለጠ ማብራሪያ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አበገደ ፊደልና ፊደል ዋሪያ 1934 ተመለወከቱ፡፡

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ስለግዕዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም ፊደላት ታሪክ ለውጥና ጠቀሜታ ተመለክተናል፡፡ ስለዚህ ለምዕራፉ ማጠቃለያ የሚሆኑ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ስሩ፡፡

1. የሥነ ልሳን ምሁራን ግዕዝ ቋንቋ አፉን የሚፈታበት ትውልድ ስሌለ ከሞቱ ቋንቋዎች ውስጥ ይመዳባል ይላሉ፡፡ እናንተስ በምዕራፉ ከተማረነውና የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ ቋንቋው አለ ወይስ ሙቷል? መልሳችሁ አለም ይሁን ሙቷል ለመረጣችሁት መልስ ከአምስት በላይ ማስረጃዎች (አመክንዮ) አስቀምጡ?
2. በግዕዝ ቋንቋ ተመሳሳይ ድምጽና የተለያየ ቅርጽ ያላቸው ሞክሸ ፊደላት አሉ እነዚህ ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው ፊደላት ይቀነሱ አይቀነሱ ክርክር እንዳለባቸው ከላይ ተመለክተናል እናንተም አንዱን ደግፋችሁ ለደገፋችሁት ሀሳብ ቢያንስ ስምንት  ምክንያት አስቀምጡ?

**ምዕራፍ ፪**

**፪. የግዕዝ ቋንቋ ክፍላተ ቃላት (የቃል ክፍሎች)**

**ስለግዕዝ ቋንቋ የቃል ክፍሎች በሰፊው እንዳልተጠና አንዳንድ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡እንደ በላይ ገለጻ የግዕዝ የቃል ክፍሎች የምንላቸው ሰባት ናቸው፡፡**

**፩.ስም**

**፪. ተውላጠ ስም**

**፫. ግስ**

**፬. ቅጽል**

**፭. መስተዋድድ**

**፮.. መስተጻምር**

**፯. ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡**

**፩. ስም ስም ሰመየ (ቀተ) ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ስም አወጣ፣ ሰየመ ማለት ነው ስም በሶስት ምድቦች ይከፈላል፡፡**

**ሀ. ውልድ ስም፡- ማለት ከግስ ርባታ የሚገኝ (የሚወጣ) ስም ነው፡፡ በሌላ አባባል ዘር በመባል (መድ) ይታወቃል ለምሳሌ ቀትል/አገዳደል/ የቀተለ ዘመድ ዘር ነው፡፡**

**መቅደስ (መቀደሻ ቦታ) የቀደሰ ባዕድ ዘር ነው፡፡ ስብሐት(ምስጋና) የሰብሐ ምዕላድ ዘር ነው፡፡**

**ለ. ነባር ስም ከግስ፡- ከርባታ የማይገኝና ለግስ ርባታም ዘር የማይሆን ነባር የማይናወጥ ቃል ማለት ነው ፡፡ ምሳሌ ማይ፣ እሳት፣ ምኩራብ፣ ኮከብ፣ ወርኅ፣ ዓለም፣ ፀሀይ፣ ገነት ምድር ወዘተ.**

ሐ. ስመ ተጸውዖ (የመጠሪያ ስም) መጠሪያ ስሞች የአንድ የታወቀ ነገር ሰው ወይም መልካዓ ምድር መጠሪያዎች ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ የመጠሪያ ስሞች ከነባር ስሞች የሚመደቡ ሲሆን አንዳንድ የመጠሪያ ስሞች ደግሞ ከግስ ርባታ የሚወጡ ናቸው፡፡

ምሳሌ ከቀደሰ ግስ ቅድስት

ከሠሐቀ (ሣቀ) ግስ ይሥሓቅ

ከሰብሐ ግስ ስቡህ ወዘተ.ስሞችን ከግስ ርባታ ስናገኝ እንደ አቤል፣ሄኖክ፣ሙሴ ያሉ የተጸውዖ ስሞችን ከነባር ስም እናገኛለን፡፡

፪. ተውላጠ ስም፡- የምንለው በስም ቦታ ተተክቶ የሚያገለግል ነው፡፡ አስሩ መራሕያን በስም ቦታ ተተክተው የሚነገሩ የርባታ መደቦች ናቸው፡፡ እነሱም በወንድና በሴት በሩቅና በቅርብ በነጠላና በብዙ የሚነገረውን ርባታ ያሳያሉ፡፡ ተውላጠ ስሞች አስር ናቸው

አነ (እኔ) አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር

ንህነ (እኛ) አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር

አንተ ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ወንድ ጾታ

አንቲ/አንች) ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ሴት ጾታ

አንትሙ/እናንተ) ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ወንድ ጾታ

አንትን (እናንተ) ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሴት ጾታ

ወእቱ(እሱ) ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ወንድ ጾታ

ይእቲ (እሷ) ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ሴት ጾታ

ውእቶሙ(እነሱ) ሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ወንድ ጾታ

ውእቶን (እነሱ) ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ሴት ጾታ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የግዕዝ የቃል ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑና በተለይ ደግሞ ስለ ስምና ተውላጠ ስም ተመለክተናል፡፡

✓ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ጠንክሮ መያዝን የሚጠይቁ የአንድ ቋንቋ ክፍሎች ቃላትና የግስ ስልቶች ናቸው፡፡ አማርኛና ሌሎች የሴሜቲክ ቋንቋ ተናጋሪና ሰሚ ደግሞ ብዙዎቹን የግዕዝ ቃላት ያውቃቸዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አማርኛ ብዙ ቃላትን ከግዕዝ እንዳለ ስለወሰደ ነው፡፡

ምሳሌ መጽሐፍ፣ ሰማይ፣ ምድር፣ ጸጋ፣ ፀሀይ፣ ምሳሌ፣ ዐይን፣ ነፋስ፣ ነፍስ፣ ሥጋ፣ መንፈስ፣ ሕሊና፣ ሞት፣ አሳ አንበሳ፣ ቤት ወዘተ. የሚሉት አማርኛ እንዳለ ከግዕዝ የወሰዳቸው ቃላት ናቸው፡፡ አማርኛ ብዙዎችን ቃላት ከግዕዝ እንዳለ ሲወስድ አንዳንዶቹን ደግሞ ትንሽ ለውጥ በማድረግ ወስዷል፡፡

ምሳሌ ሰምዐ ሰማ

መጽአ መጣ

ሐዲስ አዲስ

እድ እጅ

እንዲህ ዓይነት ለውጦችን አማርኛ ተናጋሪ በሚከተሉት ህጎች መያዝ ይችላል፡፡

፩. በግዕዝ ቋንቋ ሀ፣ሐ፣ኀ በቃል መጀመሪያ ሲመጡ በአማርኛ ወደ ‹አ› ይለወጣሉ፡፡

ምሳሌ፡-

| <u>ግዕዝ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ኀተመ | አተመ |
| ሐለመ | አለመ |
| ሐረሰ | አረሰ |
| ሀገር | አገር |
| ሐዲስ | አዲስ |
| ኀደረ | አደረ |

ሐመድ    አመድ

፪. በግዕዝ ‹አ› እና ‹ዐ› በቃል መጀመሪያ ካልመጡና በቃል መጨረሻ ከመጡ ቀዳሚያቸውን ፊደል ራብዕ አናባቢ ይሆኑትና ራብዕ አድርገውት ይጠፋሉ፡፡

ምሳሌ

| <u>ግዕዝ</u> | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|
| ለምአ | ለማ |
| መልአ | መላ |
| ሥርዐ | ሰራ |
| ኀጥአ | አጣ |
| ሰምዐ | ሰማ |
| ረግዐ | ረጋ |
| ገብአ | ገባ |
| ሥዐለ | ሣለ |
| ጠፍአ | ጠፋ |

፫. በግዕዝ ሀ፣ሐ.ኀ በአማርኛ ወደ ‹አ› ይለወጣሉ ብለናል እነዚህ ሀ፣ሐ፣ኀ ዎች ወደ ‹አ› ከተቀየሩ በኋላ ደግሞ በሁለተኛው ተራ ቁጥር እንዳየነው ራብዕ አናባቢ ሆነዉት ቀድሚቸው የመጣውን ፊደል ራብዕ አድረገውት ይጠፋሉ፡፡

ምሳሌ

| <u>ግዕዝ</u> | | <u>አማርኛ</u> |
|---|---|---|
| መርሐ | መርአ | መራ |
| ሰርሐ | ሰርአ | ሰራ |
| ሰፍሐ | ሰፍአ | ሰፋ |

ሰሐበ ሰአበ ሳበ

ረኀበ ረአበ ራበ

ሠብሐ ሠብአ ሠባ

መሐለ መአለ ማለ

፬. በግዕዝ የ ጸ እና ፀ ድምጽ በአማርኛ ወደ ጠ ይለወጣል እዚህ ላይ ግን ሁሉም የ ጸእና ፀ ድምጽ በአማርኛ ወደ ጠ ይለወጣል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡ምክንያቱ ደግሞ ‹ጠ› ፊደል በሁለቱም ቋንቋዎች ስላለ ነው፡፡

ምሳሌ

| ግዕዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ጸምአ | ጠማ |
| መጽአ | መጣ |
| ወጽአ | ወጣ |

የጸ እና ፀ ጉዳይ በአንዳንድ ተናጋሪዎች አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ፊደላት በግዕዝም በአማርኛም አሉ፡፡ ሰለጠን ያሉ ተናጋሪዎች ጠ በሚያስፈልግበት ቦታ ሁሉ ጸ፣ፀ ን እየተኩ ይናገራሉ፡፡ ምሳሌ ጸባይ የሚል ቃል በግዕዝም በአማርኛም የለም በሁለቱም ቋንቋ ትክክለኛው አነጋገር ጠባይ ነው በማለት ጌታቸው ኃይሌ ያብራራሉ፡፡

አማርኛ ማወቃችን ግዕዝን ለመማር ቢረዳንም ጣልቃ እየገባ እንደሚያስቸግረንም አውቀን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ጣልቃ የሚገባው በሁለት መንገድ ነው፡፡

፭. ግዕዝና አማርኛ ተመሳሳይ ቃል ኖሯቸው በአነባብ ግን ይለያያሉ፡፡

ከዚህ በታች ያለው ምሳሌ በግዕዝ ላልቶ የሚነበብ ሲሆን አማርኛ ተናጋሪዎች ግን አጥብቀው ይናገሩታል፡፡

ምሳሌ

| ግዕዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ባረከ | ባረከ |
| ሰረቀ | ሰረቀ |
| ሰገደ | ሰገደ |
| አንበሳ | አንበሳ |

አማርኛ ከግዕዝ የራቀበት ሌላው መንግድ አናባቢ /vowel/ የሌለውን ሳድስ ባለ አናባቢ በማድረግ ነው፡፡

ምሳሌ

| ግዕዝ | አማርኛ |
|---|---|
| ግብር | ግ-ብ-ር |
| ፍትህ | ፍ-ት-ህ |
| ተክል | ተ-ክ-ል |
| ደብር | ደ-ብ-ር |
| ምድር | ም-ድ-ር |
| ገድል | ገ-ድ-ል |

፩.፩. ፍኖተ ንባብ ዘልሳነ ግዕዝ (የግዕዝ ቋንቋ የንባብ መንግድ)

እንደ አብዛኛዎቹ ምሁራን ገለጻ ዓበይት የግዕዝ ቋንቋ የንባብ መንገዶች አራት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

፩. ተነሽ ንባብ

የቃሉ መጨረሻ ፊደል ኀምስ እና ሳድስ ከሆነው በስተቀር ቀሪዎቹ አምስት ፊደላት የቃል መጨረሻ ፊደል ሆነው ሲመጡ ከፍ ባለ ድምጽ (እየተነሡ) ይነበባል፡፡ የቀዳማይ አንቀጽ

ግስ አይነቶች መድረሻ ቀለማት ሁሉም በሚባል መልኩ ግዕዝ ሲሆን በኃምስ ይቤ የተባለው ግስ ይደርሳል በዚህ መሰረት ግስ በሙሉ ተነሽ ነው፡፡

ምሳሌ ገብረ፣ሐሙ፣ሖሪ፣ ሖራ፣ ሀቦ፤ ነበረ፣ ሀበነ፣ ተዘከረኒ…

፪ ሰያፍ ንባብ የምንለው በመድረሻ ፊደሉ ተጣይን (በሳድስ) መስሎ በአነባቡ ደግሞ ተነሽን መስሎ የሚሄድ የንባብ ስርዓት ነው፡፡

ምሳሌ በአንቀጽ የሐውር፣ ይነብር፣ ይቀውም

በስም፡-ጳውሎስ ፣ዘካርያስ፣ኢሳይያስ

ዓ.ነገር ወይሰመይ ስሙ አማኑኤል

ወትትሐነጽ በፈለገ ጤግሮስ

፫. ተጣይ ንባብ በመድረሻ ፊደሉ ሰያፍን መስሎ (ሳድስ) በአነባቡ ደግሞ ወዳቂን መስሎ የሚነበብ ነው፡፡

ምሳሌ በዘር በነባር እኩት፣ስብሕት፣ሐመር በስም ማርያም፣ አዳም፣ ሚካኤል….

ዓ. ነገር. እግዚአብሔር ዓቢይ ዘለዓለም

፬. ወዳቂ ንባብ፡-በሰባቱም ፊደላት የሚደርስ ሆኖ በአነባቡ ተጣይን የሚመስል ነው፡፡

ምሳሌ በግዕዝ አሐተ፣ክልኤተ በካዕብ አሐዱ ክልኤቱ በሣልስ ኀዳሪ፣ነባሪ፣ዘምሪ በራብዕ መና ደመና፤ በኃምስ ሙሴ ስላሴ፤ በሳድስ ዝ ፤በሳብዕ ከበሮ መሰንቆ ደማስቆ ወዘተ ይላል፡፡ምሳሌ ዐሠርተ ወክልኤተ

ሠለስተ አስማት

ብእሴ ጻድቀ

ዝ ውእቱ መጽሐፍ

ወበጽሐ ጳውሎስ ሀገረ ደማስቆ

ማስታወሻ ወዳቂና ተነሽ መድረሻቸው ይመሳሰላል ያለው አማራጭ የትኛው እንደሚነሳ የትኛው እንደሚወድቅ ማጥናትና መለየት ብቻ ነው፡፡

**ንዑሳን የግዕዝ ቋንቋ የንባብ መንገድ**

ቋሚ ምድባቸው ከላይ በተመለከትናቸው አራት ዐበይት ንባባት ውስጥ የሆነ ልዩ ልዩ አነባብ ዓይነቶች ናቸው፡፡

ሀ. ጠባቂ(ማጥበቅ) ይህ ስርዓት ንባብ በቃሉ ውስጥ የሚጠብቅ ፊደል ኖሮ ቃሉ ጠብቆ እንዲነበብ የሚያደርግ ነው፡፡

ምሳሌ ቀደሰ፣ሐዳግ፣ይቀትል፣ነጸረ፣ ተዘከሮ

ለ. ልሕሉሕ (ልል) ማላላት በቃሉ ውስጥ የሚጠብቅ ፊደል ከሌሌ ንባቡ ላልቶ ይነበባል፡፡

ምሳሌ ቀተለ፣ ነበረ፣ ገብረ፣ ፈጠረ....

ሐ. ተናባቢ የምንለው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቃላት(ስሞች) እንደ አንድ ሆነው (ተያይዘው) ሲናበቡ ነው፡፡ ጌታቸው ገጽ 88 ተመልከቱ

መ. ቀዋሚ (ኢተናባቢ) ይህ ንባብ በዓ.ነገር ውስጥ  ሁለትና ከዚያ በላይ ቃላት ሳይናበቡ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙበት የንባብ አይነት

ምሳሌ አክብር አባከ ወእምከ፣ መጽአ ወልድ፣

ሠ. መዋጥ ከቃሉ ውስጥ ያለ ፊደል ሳይጎላ በውስጠ ታዋቂነት የሚነበብበት ስርዓት ነው፡፡

ምሳሌ ወይን፣ ኤልሳዕ፣ድንግል

ረ. መቁጠር በዚህ ስርዓተ ንባብ በአንድ ቃል ውስጥ የሚገኙ ፊደላትን በሙሉ ያለመዋጥ ማንበብ ማለት ነው፡፡ ወእቱ፣ይእቲ፣ ትማልም

ማሳሰቢያ አብዛኛዎቹ ተነሽ አነባቦች ግስና ከግስ የወጡ ቃላት ሲሆኑ ተጣይ ደግሞ ስሞች ናቸው፡፡

***መራሕያን***

***መራሕያን የሚለው ብዙ ቁጥር መርሐ( መራ) ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም መሪዎች ማለት ነው፡፡ በግዕዝ ቋንቋ መራሕያን የሚባሉት ከላይ ያየናቸው አስሩ ናቸው፡፡ እነዚህም***

***አነ፣ንሕነ ፣አንተ፣አንቲ፣አንትሙ፣አንትን፣ውእቱ፣ይእቲ፣ ውእቶሙ፣ውእቶን ናቸው፡፡***

***መራሕያን መሪዎች የተባሉበት ስለ ሶስት አገልግሎታቸው ነው፡፡***

**፩. እንደ ምድብ ተውላጠ ስም (pronouns) ስለሚያገለግሉ**

***መራሕያን እንደ ተውላጠ ስም በመሆን በስም ፈንታ ተተክተው ያገለግላሉ፡፡እነሱም ስም*** **የስም አጻፋ እየሆኑ በወንድና በሴት በሩቅና በቅርብ በነጠላና በብዙ የሚነገረውን ያሳያሉ፡፡**

**አስሩ *መራህያን* በሶስት *መደብ ይመደባሉ*፡፡**

***ቀዳማይ መደብ /አንደኛ መደብ/*** 1st person / **የወል ጾታ**

**አነ  እኔ** I **ነጠላ**

**ንህነ  እኛ** We **ብዙ**

**፪. ካልዓይ *መደብ/*ሁለተኛ *መደብ/*** 2nd person

| | | |
|---|---|---|
| **አንተ** | **አንተ** | you |
| **አንቲ** | **አንቺ** | ›› |
| **አንትሙ** | **እናንተ** | ›› |
| **አንትን** | **እናንቺ** | ›› |

**፫. ሣልሳይ *መደብ* /ሶስተኛ *መደብ*** /3rd person/

| | | |
|---|---|---|
| **ውእቱ** | **እሱ** | He |
| **ይእቲ** | **እሷ** | She |
| **ውእቶሙ** | **እነሱ** | They |

ውእቶን    እነርሱ    ››

**እነዚህን መራሕያን ከግስ ጋር በማዛመድ እንመልከት**

ግስ፡- ሰገደ (ሰገደ)፣ ቀደሰ (አመሰገነ)፣ኖመ (ተኛ)፣ ነበረ (ተቀመጠ)፣ ሖረ (ሄደ) ፣ሰበከ (ሰበከ)፣ ወድቀ (ወደቀ)፣ ኀደገ (ተወ)

አነ ሰገድኩ፣ቀደስኩ፣ ኖምኩ፣ ነበርኩ፣ ሖርኩ፣ ሰበኩ፣ ወደቁ፣ኀደጉ፣

ንህነ ሰገድነ፣ ቀደስነ፣ኖምነ፣ነበርነ፣ሖርነ፣ ሰበክነ፣ ወደቅነ፣ኀደገነ

አንተ ሰገድከ፣ ቀደስከ፣ኖምከ፣ነበርከ፣ሖርከ፣ ሰበከ፣ ወደቀ፣ ኀደገ

አንቲ ሰገድኪ፣ቀደስኪ፣ኖምኪ፣ነበርኪ፣ሖርኪ፣ሰበኪ፣ወደቂ ኀደጊ

አንትሙ ሰገድክሙ፣ቀደስክሙ፣ኖምክሙ፣ነበርክሙ፣ሖርክሙ፣ሰበክሙ፣ወደቅሙ፣ኀደግሙ

አንትን ሰገድክን፣ቀደስክን፣ኖምክን፣ነበርክን፣ሖርክን፣ሰበክን፣ወደቅን፣ኀደግን

ወእቱ ሰገደ፣ ቀደሰ፣ኖመ፣ነበረ፣ ሖረ፣ሰበከ፣ ወድቀ፣ ኀደገ

ይእቲ ሰገደት፣ቀደሰት፣ኖመት፣ነበረት፣ሖረት፣ሰበከት፣ወድቀት፣ኀደገት

ውእቶሙ ሰገዱ፣ቀደሱ፣ኖሙ፣ነበሩ፣ሖሩ፣ሰበኩ፣ወድቁ፣ኀደጉ

ውእቶን ሰገዳ፣ቀደሳ፣ኖማ፣ነበራ፣ሖራ፣ሰበካ፣ወድቃ፣ኀደጋ

ማስታወሻ የግስ መጨረሻ ፊደል ከ፣ቀ፣ገ ከኖነ መዘርዘርያውን ‹‹ከ›› ን ይውጡታል፡፡

**፪. መራሕያን እንደ ነባር አንቀጽ /verb to be/**

ነባር አንቀጽ ሲባል ማሰሪያ ግስ ማለት ነው፡፡ መራሕያንም በአንቀጽነታቸው እየተተረጎሙ ሲፈቱ ማሰሪያ ይሆናል፡፡

ውእቱ ነው፣ሆነ፣ነበር፣ኖረ

ይእቲ ናት፣ነበረች

ውእቶሙ ነበሩ፣ናቸው /ወ/

ውእቶን ነበሩ፣ናቸው/ሴ/

አንተ ነህ፣ነበርክ

አንቲ ነሽ፣ነበርሽ

አንትሙ ናችሁ ነበራችሁ/ወ/

አንትን ናችሁ ነበራችሁ/ሴ/

ንህነ ነበርን ነን

አነ ነኝ ነበርኩ

ምሳሌ አነ ውእቱ ግንደ ወይን (የወይን ግንድ እኔ ነኝ)፣ አነ ውእቱ ረድእ (እኔ ተማሪ ነኝ). ቅድስት ወናሆም አርድእት ውእቶሙ (ቅድስትና ናሆም ተማሪዎች ናቸው)፡፡

ማስታወሻ ውእቱ የለዋጭ የተለዋጭ ባህሪ ስላለው በተባዕትና በአንስት በብዙና በነጠላ ይፈታል /መጠቀም/ ይቻላል፡፡

፫. መራህያን እንደ አመልካች ቅጽል

መራሕያን ሌላው ሶስተኛው አገልግሎታቸው አንድን ነገር ወይም አካል በተባዕትና በአንስት በማይታይና በሚታይ፣ በቅርብ ሩቅና በቅርብ ቅርብ አመልካች ጠቋሚ እየሆኑ መነገራቸው ነው፡፡በሶስት መንገድ ይቀርባሉ

ተናጋሪን እኔ አነ

የማይታይ ውእቱ

የሚታይ  ውእቱ

ይእቲ    ያች

ውእቶሙ እኒያ

ውእቶሙ እኒያ ውእቶን እኒያ

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው መራሕያን ሶስት አገልግሎት አላቸው ተውላጠ ስም መሆን፣ ማሰሪያ አንቀጽ መሆንና አመልካች ቅጽል መሆን ናቸው፡፡

## ፫. ግስ

በቋንቋ ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡በግዕዝ ቋንቋ ግስ /ዘር/ በመባልም ይታወቃል፡፡ ዘር የተባለበት ምክንትም ዘር የግስ ጥንት የርባታ መሰረት ስለሆነ ነው፡፡ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948) ዘር መባሉም በምሳሌ ነው ይላሉ፡፡ ይኸውም ዘር አንዱን ቅንጣት በዘሩት ጊዜ ብዙ ቅንጣቶችን እንደሚያፈራ ዘርም/ግስም/ አንዱን ባረቡት /በገሰሱት/ ጊዜ አንዱ ግስ ብዙ ቃላትን ስለሚያፈራ ነው፡፡ በአጠቃላይ ግስ ማለት የቋንቋ ጓዝ የዘርና የነባር እክት ወይም እቃ ግሴት ማለት ነው ይላሉ፡፡ ግስ የምንላቸው በግዕዝ ከ ‹ሀ-ፐ› የሚደረደሩ የተለያዩ ቃላት ናቸው፡፡ እነዚህም እንደ አርእስተ ግሳቸው የአረባብ ዘዴ ይረባሉ፡፡

የግዕዝ ግስ የሚነሳባቸው ቀላማት አምስት ናቸው፡፡እነዚህም ግዕዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ እና ሳብእ ናቸው፡፡ ስለዚህ የግዕዝ ግስ በካዕብ እና በሳልስ አይነሳም ወይም አይጀምርም፡፡ የግስ መድረሻ ቀለማት በአብዛኛው ግዕዝ ሲሆን በኃምስ ይቤ የተባለው ነባር ብቻ ደርሳል ወይም ይጨርሳል፡፡

ምሳሌ እንመልከት በግዕዝ የሚጀምሩ፡- ቀተለ/ገደለ/፣ ቀደሰ እና ተንበለ ሲሆኑ በራብዕ የሚጀምሩ፡- ባረከ/ባረከ/ እና ማህረከ ናቸው፡፡ በኃምስ ሴሰየ/መገበ/ በሳድስ ክህለ/ቻለ/ እና በሳብእ ጦመረ/ጻፈ/ የተባሉት ግሶች ይጀምራሉ፡፡ እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ምሳሌዎች በአምስቱ ፊደላት /ቀለማት/ የጀመሩ ሲሆን የጨረሱት ደግሞ በግዕዝ ወይም በመጀመሪያ ፊደል ብቻ ነው፡፡ በኃምስ /አምስተኛ/ ፊደል የሚጨርሰው ግን ነባር የሆነው ይቤ/ አለ) የተሰኘው ግስ ብቻ ነው፡፡

ነባር የምንለው ዘርነት የሌለው ከአንቀጽ የማይገኝ የቋንቋ ቤተሰብ እየሆነ የሚገኝ ጥሬ ቃል ሁሉ ነባር ይባላል፡፡

## 2.1. አርእስተ ግስ (የግስ አርእስት/

**ጥያቄ፡- ስለ ግዕዝ ግስ ምንነትና ስለ ግስ አርእስቶች ከተለያዩ መጻሕፍት በመፈለግ አብራሩ?**

አርእስተ ግስ ትርጉሙ የግስ ራሶች፣ አለቆች እና ፊታውራሪዎች ማለት ነው፡፡ አርእስተ ግስ መባላቸውም ከ ‹ሀ-ፐ› ላሉት ግሶች ጠቅላዮች ስለሆኑና እነዚህ ከ ‹ሀ-ፐ› ያሉት ግሶች በእነዚህ የግስ አርእስት የርባታ ዘዴ ስለሚረቡ አርእስተ ግስ ተብለዋል፡፡ የግስ አርእስት የምንላቸው እንደየምሁራኑ አከፋፈላቸው የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948) የግስ አርእስትን በሰባት ይከፍሏቸዋል እነዚህም ቀተለ፣ ቀደሰ/አመሰገነ/ ፣ ዴገነ፣ ኖለወ(ጠበቀ)፣ ደንገፀ /ደነገጠ/ ማህረከ/ማረከ/ ናቸው ይላሉ፡፡

ያሬድ ሽፈራው /2007/ ደግሞ የግስ አርእስትን በስምንት ይከፈሏቸዋል፡፡ እነዚህም ቀተለ፣ ቀደሰ፣ተንበለ/ለመነ/ ባረከ፣ ማህረከ፣ ሴሰየ፣ ክህለ፣ ጦመረ በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡

እንደ ጌታቸው ኃይሌ /2008/ ገለጻ ደግሞ የግስ አርእስት /የግስ ስሮች/ ሶስት ናቸው እነዚህም ቀተለ የላላ ባለሶስት ፊደል፣ ቀደሰ የጠበቀ ባለ ሶስት ፊደል፣ ባረከ ባለሶስት ቀለም በራብእ የተነሳ ግስ ነው፡፡እነዚህ አርእስተ ግሶች በእነሱ ዘዴ የሚራባ ሰራዊት አላቸው፡፡

**የግስ ርባታ( ርባታ ስሞች) ሶስት ናቸው፡፡ እነዚህም**

1. **ሀ. ዐቢይ ርባታ** የምንላቸው ሶስት ናቸው እነዚህም ቀዳማይ አንቀጽ (ኃላፊ ጊዜ)፣ ካልዓይ አንቀጽ ( የትንቢት ጊዜ)አ እና ራብዓይ አንቀጽ (ትዕዛዝ) ናቸው፡፡ዐቢይ የተባሉበት ምክንያትም ዐ.ነገር ስለሚያስሩና ስለሚስቡ ነው፡፡

አርእስተ ግሶችን በእነዚህ ዐቢይ ርባታዎች እና በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ወንድ ጾታ (ውእቱ) ሲገለፁ እንደሚከተለው በምሳሌ እንመልከት

| ኃላፊ | ትንቢት | ትዕዛዝ |
|---|---|---|
| 1. ቀተለ /ገደለ/ | ይቀትል /ይገድላል/ | ይቅትል/ይግደል/ |
| 2. ቀደሰ | ይቄድስ | ይቀድስ |
| 3. ተንበለ | ይተነብል | ይተንብል |
| 4. ባረከ | ይባርክ | ይባርክ |
| 5. ማህረከ | ይማህርክ | ይማህርክ |
| 6. ሴሰየ | ይሴሲ | ይሴሲ |
| 7. ክህለ | ይክህል | ይክህል |
| 8. ጦመረ | ይጦምር | ይጦምር |

ከዚህ ከነጠላ ቁጥር ወንድ ጾታ በተጨማሪ በአስሩም ተውላጠ ስሞች እነዚህ አርእስተ ግሶች በኃላፊ ጊዜ ሲገሰሱ (ርባታቸውን) እንመልከት

አነ ቀተልኩ፣ቀደስኩ፣ተነበልኩ፣ባረኩ፣ማህረኩ፣ሴሰይኩ፣ከሀልኩ፣ጦመርኩ

ንህነ ቀተልነ፣ቀደስነ፣ተነበልነ፣ባረክነ፣ማህረክነ፣ሴሰይነ፣ከሀልነ፣ጦምርነ

አንተ ቀተልከ፣ቀደስከ፣ተነበልከ፣ባረከ፣ማህረከ፣ሴሰይከ፣ከሀልከ፣ጦመርከ

አንቲ ቀተልኪ፣ቀደስኪ፣ተነበልኪ፣ባረኪ፣ማህረኪ፣ሴሰይኪ፣ከሀልኪ፣ጦመርኪ

አንትሙ ቀተልክሙ፣ቀደስክሙ፣ተነበልክሙ፣ባረክሙ፣መሀርክሙ፣ሴሰይክሙ፣ከሀልክሙ፣ ጦመርክሙ

አንትን ቀተልክን፣ቀደስክን፣ተነበልክን፣ባረክን፣መሀርክን፣ሴሰይክን፣ከሀልክን፣ጦመርክን

ውእቱ ቀተለ፣ቀደሰ፣ተንበለ፣ባረከ፣ማህረከ፣ሴሰየ፣ክህለ፣ጦመረ

ይእቲ ቀተለት፣ቀደሰት፣ተንበለት፣ባረከት፣ማህረከት፣ሴሰየት፣ክህለት፣ጦመረት

ውእቶሙ ቀተሉ፣ቀደሱ፣ተንበሉ፣ባረኩ፣ማህረኩ፣ሴሰዩ፣ከሀሉ፣ጦመሩ

ውእቶን ቀተላ፣ቀደሳ፣ተንበላ፣ባረካ፣ማህረካ፣ሴሰያ፣፣ከሀላ፣ጦመራ

ለ. ንዑስ ርባታ፡ የምንላቸው  አምስት ናቸው እነዚህም ዘንድ አንቀጽ፣ አርእስት ንዑስ አንቀጽ፣ ቦዝ፣ ውስጠ ዘ እና ሳቢ ዘር ናቸው

| ሳልሳይ/ዘንድ | አርእስት | ቦዝ | ውስጠ ዘ | ሳቢ ዘር |
|---|---|---|---|---|
| ይቅትል | | ቀቲሎ | | |
| ይቀድስ | | ቀድሶ | | |
| ይተንብል | | ተንብሎ | | |
| ይባርክ | | ባርኮ | | |

ሐ. ደቂቅ ርባታ፡ እነዚህም ዘርና ነባር ናቸው፡፡

**የግዕዝ አስራው (አብዥ) ቀለማት**

በግዕዝ ቋንቋ አብዥ ቀለማት (ነጠላ ቁጥርን ወደ ብዙ) የሚለውጡልን ቀለማት አስራው ቀለማት ይባላሉ፡፡ እነዚህም ለ፣መ፣ተ፣ነ፣አ፣ወ፣የ ናቸው፡፡

1. የለ ማስረጃ ኪሩብ-ኪሩቤል

   ሱራፊ -ሱራፌል

2. የ‹መ› ማስረጃ ኩሉ-ኩሎሙ፤አንተ አንትሙ..
3. የ‹ተ› ማስረጃ ህጻን-ህጻናት፤ካህን-ካህናት፤አናብስት
4. የ‹ነ› ማስረጃ ኄር-ኄራን፤ጻድቅ-ጻድቃን
5. የ‹አ› ማስረጃ ደብር-አድባር፤ሀገር -አሕጉር፤ህዝብ-አህዛብ
6. የ‹ወ› ማስረጃ እድ-እደው፤አብ-አበው፣
7. የ‹የ› ሌሊት ለያልየ

   መሬት መራዕይ

**ምዕራፍ ሶስት**

**፫. የግዕዝ ዐ.ነገር አወቃቀር**

**፫.፩.** **የግዕዝ አወንታዊ ዐ.ነገር፡-** ሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎችን ጨምሮ ግዕዝ በአረፍተ ነገር አወቃቀሩ ለየት ያለ ስልት የተከተለ ነው፡፡ይኸውም ግዕዝ ባለቤቱንና ግሱን እንዲሁ ጎን ለጎን ያለ ማሚያም በማሚያም ያስቀምጣቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የግዕዝ ዐ.ነገር አወቃቀር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

1. **ባለቤት + መሙያ (ግስ)**

ምሳሌ አበበ መምህር (አበበ መምህር ነው፡፡)

ሶስና ሰናይት (ሶስና ቆንጆ ናት፡፡)

ቴዎድሮስ ንጉሥ (ቴዎድሮስ ንጉሥ ነው፡፡)

ጥናታዊ የግዕዝ ዐ. ነገር አወቃቀር ይህ የመጀመሪያው ባለቤት + መሙያ የሚለው እንደነበረ ሌሎች አወቃቀሮች የሌሎች ቋንቋዎች ተጽእኖ እንደሆነ ጌታቸው ኃይሌ (2008) ይገለጻሉ፡፡ በእዚህ በመጀመሪው አወቃቀር ‹ነው› የሚለው ነባር ማሰሪያ በውስጥ ታዋቂነት ይታወቃል እንጅ አይጻፍም ማለትነው

2. **ባለቤት+ መሙያ + ነባር ማሰረያ**

ምሳሌ አበበ መምህር ውእቱ (አበበ መምህር ነው፡፡)

ሶስና ሰናይት ይእቲ (ሶስና ቆንጆ ናት፡፡)

ቴዎድሮስ ንጉሥ ውእቱ (ቴዎድሮስ ንጉሥ ነው፡፡)

አበበ ወአስቴር መምህራን ውእቶሙ አበበ እና አስቴር መምህራን ናቸው፡፡

3. **መሙያ+ ነባር ማሰሪያ +ባለቤት**

መምህር ውእቱ አበበ (አበበ መምህር ነው፡፡)

ሰናይት ይእቲ ሶስና (ሶስና ቆንጆ ናት፡፡)

ንጉሥ ውእቱ ቴዎድሮስ (ቴዎድሮስ ንጉሥ ነው፡፡)

ማስታወሻ፡- ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው የዐ.ነገር አወቃቀሮች ውስጥ ሁለተኛውና ሶስተኛው ልዩነታቸው የቃላት አደራደር ቅደም ተከተል መቀያየር ብቻ መሆኑን እናሰተውል፡፡ በሌላ መልኩ ነባር ማሰሪያ የምንላቸው ከላይ መራሕያን እንደማሰረያ አንቀጽ በተሰኘው ርዕስ ያየናቸው ሲሆኑ አስሩ መራሕያን ሲሆኑ እነዚህ ሁላቸውም ዐ.ነገር ማሰር ይችላሉ፡፡ ውእቱ የተሰኘው ነባር ማሰሪያ አንቀጽ ግን ከእነዚህ በተለየ በአስሩም ተውላጠ ስሞች እየገባ ዐ.ነገር ማሰር ይችላል፡፡

**፫.፪. አሉታዊ የግዕዝ ዐ.ነገር**

የታወቁ የግዕዝ ቋንቋ አሉታዎች የምንላቸው አል፣ አኮ ፣እና ኢ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

| <u>አወንታዊ ዐ.ነገር</u> | <u>አሉታዊ ዐ.ነገር</u> |
|---|---|
| 1. ቦ መጽሐፍ (መጽሐፍ አለው (አለ) | አልቦ መጽሐፍ (መጽሐፍ የለውም(የለም) |
| 2. ጳውሎስ መምህር(ጳውሎስ መምህር ነው) | አኮ መምህር ጳውሎስ (ጳውሎስ መምህር አይደለም፡፡) |
| 3. ሖረ ኀበ አዲስ አበባ (ወደ አ.አ ሄደ) | ኢሖረ ኀበ አዲስ አበባ ( ወደ አ.አ አልሄደም) |

**፫.፫ መጠይቃዊ ዐ.ነገር**

በግዕዝ ዐ.ነገር ውስጥ ለመጠየቅ የሚያገለግሉን የተለያዩ ቃላት አሉ እነዚህም

| <u>ግዕዝ</u> | <u>አማርኛ</u> | ግዕዝ ዐ.ነገር | አማርኛ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1. እፎ | እንዴት | እፎ ኀደርክሙ | እንዴት አደራችሁ ? |
| 2. ምንት | ምን | ምንት ውእቱ | ምንድን ነው ? |
| 3. ለምንት | ለምን | ለምንት ሀሰስክሙ | ለምን ፈለጋችሁ ? |
| 4. ማእዜ | መቼ | ማእዜ ሖረ አበበ | አበበ መቼ ሄደ ? |

5. አይቴ    የት    አይቴ ሖረ አለሙ    አለሙ የት ሄደ?

6. እምአይቴ   ከየት    እምአይቴ መጻእኪ    ከየት መጣሽ?

**ሀ. ተማሪዎች የሚከተሉትን ቀላል የግዕዝ ዐ.ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሙ(ፈክሩ እም ልሳነ ግዕዝ ኀበ ልሳነ አምሐራ5)**

1. ውሉደ ንጉሥ ይነብሩ ውስተ ቤተ መንግሥት______________________________
2. መኑ ወእቱ ወራሴ ዘመንግሥት ኢትዮጵያ________________________________
3. ሰብአ ኢትዮጵያ ያፈቅሩ ነገሥታቲሆሙ__________________________________
4. ውእቶሙ ሰብእ ሞቱ ወተቀበሩ በዐድዋ___________________________________
5. ኢሖረት ፈትያ ኀበ አዲስ አበባ_______________________________________
6. ተሐዝን እም እመ ወልዳ ይመውት_____________________________________
7. ለምንት ሖርክሙ ኀበ ደብረ ዘይት_____________________________________
8. ዝንቱ ረድእ አብድ ሰጠጠ መጻሕፍቲሁ__________________________________
9. ሥርዋ ለጥበብ ለመኑ ተከሥተ_________________________________________
10. ኦ ወለትየ አይቴ ሀለዋ አዋልድኪ_____________________________________
11. ንጉሠ መኑ ውእቱ ዝንቱ ብእሲ_______________________________________

**ለ. ተማሪዎች የሚከተሉትን ቀላል የግዕዝ ምሳሌዊ አነጋገሮች (አንጋረ ምሳሌ ዘግዕዝ) ተመለከቱና ሌሎች የምታውቋቸውን የአማርኛ ምሳሌዊ ንግግሮች ወደ ግዕዝ ተርጉሙ (ፈክሩ)**

| አንጋረ ምሳሌ ዘግዕዝ | አማርኛ ትርጉም |
|---|---|
| 1. ኵሉ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ | ሁሉን መርምሩ መልካሙን ያዙ |
| 2. ቦ ጊዜ ለኵሉ | ለሁሉም ጊዜ አለው |
| 3. ለጠቢብሰ አሃቲ ቃል ትበቍአ | ለጥበበኛ (አስተዋይ) ሰው አንድ ቃል ይበቃዋል፡፡ |
| 4. ተሰአሎ ለአቡከ ይነግረከ፣ ወለሊቃውንቲከ ይዜንውከ | አባትህን ጠይቀው ይነግርሀል፣ መምህሮችን ጠይቃቸው ያስረዱሀል |
| 5. ተገኀሥ እም እኩይ፤ ወግበር ሰናየ | ከክፉት ራቅ መልካምንም አድርግ |
| 6. ተፋቀሩ በበይናቲክሙ | እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ |
| 7. ተፋቅሮሰ ፍጹም ህግ | ፍቅር የህግ ፍጻሜ ነው |
| 8. ንሥአ ወብልዓ ለእንታክቲ መጽሐፍ | እንካ ይችን መጽሐፍ ብላት |
| 9. አሐደ ቀለም ዘነገረከ ይኩን ከመ አቡከ ክልዔተ ቀለም ዘነገረከ ይኩን ከመ ፈጣሪከ | አንድ ቀለም የነገረህ እንደ አባትህ ሁለት ቀለም የነገረህ እንደ ፈጣሪህ ይሁን |
| 10.አክብር አባከ ወእምከ | አባትና እናትህን አክብር |
| 11. ኢታንሥእ ዘኢያንበርከ | ያላስቀመጥከውን አታንሳ |
| 12. አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሀር ጥበብ | የደግ ሰው አፍ ጥበብን ይማራል |

13.ኩኑ ጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር ፣ወየዋሃነ ከመ ርግብ እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ

የሚከተሉት ምንባቦች ከታሪክ ነገሥትና ከዜና መዋዕል የተወሰዱ ናቸው ስለሆነም በደንብ ካነበባችሁ በኋላ ርዕስ በመስጠት ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉሟቸው (ሀቡ ርዕሰ ወፈክሩ እም ልሳነ ግዕዝ ኀበ ልሳነ አምሐራ)

በ፲ወ፳፻ወ፸:ዓመተ፡ምህረቱ፡ለእግዚእነ:ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ተወልደ፡ዓጼ:ፋሲለደስ፡ወኮነ፡ስመ:አቡሁ፡ሱስንዮስ፡ወስማ፡ለእሙ፡ወልድ:ሰዓላ፡ንግሥተ፡ኢትዮጵያ፡ወሶበ በጽሐ: መዋዕሊሁ: ወሰድዎ፡ኀበ፡መምህር፡ዘሀሎ፡ውስተ፡ዓውዳ፡ለአንጾኪያ፡ ከመ፡ ይትመሀር፡ ትምህርተ፡ ቤተክርስቲያን፡ ወተምህረ፡ ምንባበ መጻሕፍት፡ ወመዝሙረ ዳዊት፡ ወሶበ፡ ኮኖ፡ ፲ወ፪፡ዓመተ፡ፈነዎ:ንጉሠ፡ነገሥት፡ሱስንዮስ፡ኀበ፡ገዳመ፡እስጢፋኖስ፡ዘውእቱ፡ዳጋ፡ለወልዱ፡ፋሲለደስ:ከመ፡ይትመሀር፡መጻሕፍተ፡ቤተክርስቲያን፡ወተምህረ፡ድሙረ፡ኩሎ:ህገ፡ወሥርዓተ መንግሥት፡፡

ወአሜሃ፡በውእቱ፡ጊዜ፡እምአመ፡ተፈልጠ፡እምኔሆሙ፡በ፷፡ዓመት፡ረከቦሙ፡በምድረ፡አምኃራ፡፡ ዘትሰመይ፡ደፋሳ፡ለብእሲቱ፡ወልድ፡ሰዓላ፡ዘስመ፡መንግሥታ፡ተሰምየት፡ሥልጣን፡ሞገሳ፡ወለወልዱ፡አቤተጉን፡ከናፍረ፡ክርስቶስ፡ወለአዋልዲሁ፡ዌዘሮ፡መለኮታዊት፡ወዌዘሮ፡ገሊላዊት፡ወዌዘሮ፡ወንጌላዊትሰ፡አሜሃ፡ነበረት፡እኀዝተ፡በእደ፡ቁርባን፡ምስለ፡እሙ፡፡

*አቤተጉን፡ፋሲለደስኒ፡ወልደ፡ንጉሥ፡እንዘ፡ወልደ፡፲ወ፮፡ዓመት፡ውእቱ፡ቀተለ፡አሜሃ፡እምኀያላነ፡ሠለስተ፡ዕደወ፡እንዘ፡ይብልዎ፡ሠለ፡ሠራዊተ፡ንጉሥ፡ኀየለ፡ኀየለ፡ወሞአ፡እምኔነ፡፡ወባሕቱ፡ኀደገ፡ለአቤተጉን፡ፋሲለደስኒ፡ውስተ፡ከተማሁ፡ደንቀዝ፡ከመ፡ይዕቅብ፡ሀገረ፡፡ወዝንቱኒ፡ወልድ፡ቡሩክ፡አቤተጉን፡ፋሲለደስ፡ዘባረኮ፡እግዚአብሔር፡ተንሥአ፡ፍጡነ… ግብረ፡ተፃብኦ፡ወተቃትሎ፡ያፈቅር፡ጥቀ፡፡…ወአቤተጉን፡ፋሲለደስኒ፡ ተመይጠ፡መንገለ፡ከተማ፡ደንቀዝ፡ወተራከበ፡ምስለ፡አቡሁ፡ወኮነ፡አሜሃ፡ትፍሥሕት፡*

ወኀሤተ፡በእንተ፡ዘተመይጠ፡ምስለ፡መዊእ፡ወኀይል፡ወከረሙ፡ሀየ፡በጥዒና፡ወበሣህል
፡፡

ወአመ፡፲ወ፱፡ዓመተ፡መንግሥቱ፡ለንጉሥ፡ሱስንዮስ፡መጽኡ፡አፍርንጅ፡እምሮም፡ወአስሐትዎ፡
ለዝንቱ፡ንጉስ፡ወአብዕዎ፡ውስተ፡ሃይማኖቶሙ..ወበዝ፡ነገር፡ተሐውከ፡ኵሉ፡ሰብአ፡ኢትዮጵያ፡ቦ
፡እለ፡ኀደጉ፡ብሔሮሙ፡ወቦ፡እለ፡ሞቱ፡በስደት፡ወተቀትሉ፡በኵናት፡ወኮኑ፡ሰማዕታት፡፻፻፡አእላ
ፋት፡ካህናት፡ወመነኮሳት፡ወማሰኑ፡ኩሎሙ፡አብያተ፡ክርስቲያናት
ወአጽንዓ፡ንጉሥ፡ሃይማኖተ፡ሮማዊተ፡ወበውእቱ፡መዋዕል፡ተንስኡ፡ላዕሌሁ፡መነኮሳ
ት፡ወሊቃውንተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ወተናገሩ፡በቅድሜሁ፡ለንጉሥ፡በድፍረት፡ውጉዘ፡ለ
ትኩን፡ሃይማኖተ፡ሮምያ፡ወትኩን፡ኅሡረ፡ወይጥፋዕ፡ዝክረ፡ስማ፡ወተሀሉ፡ተዋህዶ፡ት
ጽንዓ፡እስከ፡ለዓለም፡፡ወበተቃውሞቶሙ፡ኀልቁ፡ብዙኃን፡ሊቃውንተ፡ቤተክርስቲያን፡
ምዕመናን፡በክርስቶስ፡ወኮኑ፡ሰማዕተ፡እንዘ፡ክሉላን፡በአስይፍት፡ወበመስቀላት፡ወለብ
ዙኃን፡ተመትራ፡ልሳናቲሆሙ፡ወተሰምዓ፡ዝ ነገር፡በበሀገሩ፡፡

አቤቶሁን፡ፋሲል…ዘነበረ፡ቀዳሚ፡ደጅ፡አዝማች፡ዘስሜን፡ይቤሎ:ለአቡሁ:ሐጸጌ:ኦ፡እ
ግዚእነ:ንጉሥ:ናሁ:ኩሉ:አመጸ:ወኩሉ:ተሐውከ:በእንተ:ዝንቱ፡ነገረ:አፍርንጅ:ዘኢ.ርኢ
ነ:ወዘኢ.ሰማዕነ:ወኢ.ሀሎ:እመጻሕፍተ:አበዊነ…ሀብ:ብጽዓተ:ለእግዚአብሔር:ከመ:ት
ሚጥ:ሃይማኖተ:እስክንድርያ…ወይቤ:ንጉሥ:ኦሆ:ወእምዝ:ሜጠ:ንጉሥ:ሃይማኖተ:እስ
ክንድርያ:በአዋዲ:እንዘ:ይብል “አሚን:ይትመየጥ ወፋሲል ይንግሥ፡ ወአነሂ:
ደከምኩ::

…ለንጉሥ፡በእንተ፡ግብሩ፡እኩይ፡አምጽዓ፡እግዚአብሔር፡መዓተ፡ላዕሌሁ፡
ተአሥረ፡ልሳኑ፡ወኮነ፡ብሕመ፡ወኢ.ክህለ፡ተናገሮ፡ወደንቀዋ፡እዘኒሁ፡ወየብሳ
፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡እስከነ፡ኢ.ክህለ፡አንሶሰወ፡ወአሜሃ፡ተጸውአ፡ወልደ፡ንጉ

ሥ፡ፋሲለደስ…ወበጽሐ፡ፋሲለደስ፡ኀበ፡አቡሁ፡ወሶበ፡ርአዮ፡ደንገጸ፡ወተጽ
ቀ፡ጥቀ፡ወረከበ፡አሀደ፡ባህታዊ፡ወነገሮ፡ኩሎ፡ዘኮነ፡ላዕለ፡አቡሁ፡ወይቤ፡ባህታ
ዊ፡ምንተ፡ትገብር፡ሊተ፡በአመ፡ፈወስክዎ፡ለአቡከ፡ዳዕሙ፡ፈውሶ፡እምዝንቱ
፡ደዌ፡እኩይ፡አነ፡እሁበከ፡መንፈቀ፡መንግስቱ፡ለአቡየ፡ወአወስአ፡ባህታዊ፡ጻ
ድቅ፡እስመ፡ኢይበቁዓኒ፡መንግሥተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ኃላፊ፡ወባህቱ፡ሀለዋ፡ገ
ዳማት፡ዘተሐንፃ፡በስምየ፡ወለውእቶን፡ሀበኒ፡ርስተ፡ወጉልተ፡ከመ፡ይኩነኒ፡
ሲሳየ፡ዕለት፡ወተሰነአው፡፸ሆሙ፡ወአብጽሐ፡ፋሲለደስ፡ለጻድቅ፡ሀበ፡ቤተ፡ን
ጉሥ፡ወገብረ፡ሱባኤ፡፻መዓልተ፡ወ፻ሊያልየ፡ወሶቤሀ፡ተከስተ፡ልሳኑ፡ለንጉ
ሥ፡ወይቤ፡መንገለ፡ሀለዎት፡ትግባዕ፡ሃይማኖተ፡እስክንድርያ፡ወሀሡረ(ወሀ
ሥርተ)፡ትኩን፡ሃይማኖተ፡ሮምያ፡ይንገሥ፡በዲበ፡መንበርየ፡ወይንበር፡ፋሲ
ለደስ፡ዘአንጾኪያ…

1.1.MSQF2

አሀዱ፡ብእሲ፡ ጻድቅ፡ ተነበየ፡ ትንቢተ፡ በቅድሜሁ፡ ለንጉሥ፡ ሱስንዮስ፡ ወይቤሎ፡ በዘትነግሥ፡ ጎ ፡ወአርአየ፡ በአምሳለ፡ ኮር፡ በቅል፡ ጽሒፎ፡ ፊደለ፡ በቀዳሚሁ፡ ደ ፡ወበድኅሬሁ፡ ወ ፡ወበማዕከሉ፡ ለዘይነብር፡ ቦቱ፡ ጎ ፡ወኢያዕመረ፡ ንጉሥ፡ ትርጓሜሁ፡ አደ፡ ወሐሰሰ፡ መፈክር፡ እምድኅረ፡ ብዙ፡ ጻማ፡ ረከበ፡ አሀደ፡ ብእሴ፡ ዘኮነ፡ ወተርጎመ፡ ወዜነዎ፡ ለንጉሥ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ትርጓሜሁ፡ ወ ፡ብሂል፡ ወገራ፡ ውዕቱ፡ ደ ፡ብሂል፡ ደንቢያ፡ ኢያዕመርክዎ፡ ወኢተከስተ፡ ሊተ፡ ነገረ፡ ጎ ፡ወባህቱ፡ ሊተ፡ ይመስለኒ፡ ዘትነግሥ፡ ቦቱ፡ መካን፡ ወሀለፈ፡ ንጉሥ፡ እንበለ፡ ይትፈጸም፡ ቃለ፡ ትንቢቱ፡ እም፡ አመ፡ ነግሠ፡ ወልደ፡ ንጉሥ፡ ፋሲለደስ፡ ከመ፡ ይፈጽሙ፡ ትንቢተ፡ አቡሆሙ፡ ደክሙ፡ መጻመው፡ ብዙኃ፡ ለረኪበ፡ ጎ ፡ወገብሩ፡ ንጉሥ፡ ቤተ፡ መንግሥቶሙ፡ ጎመንጌ፡ ወበአሐቲ፡ ዕለት፡ ጠፋት፡ ፈረሶሙ፡ ለንጉስ፡ ፋሲለደስ፡ በቲካ፡ ማሰሪሃ፡ ወተረከበት፡ በዘተሐነጸ፡ ዮም፡ ቤተ መንግሥቶሙ፡ ንጉሥ፡ ፋሲለደስ፡ እንዘ፡ ትስቲ፡ ማየ፡ ውስተ፡ ፈለግ፡ ወወሰድዋ፡ ሰራዊት፡ ለፈረስ፡ ኀበ፡ ቤተ፡ ንጉሥ፡ ወነገርዎሙ፡ ሠራዊት፡ ለንጉሥ፡ ዘተረክበት፡ ቦቱ፡ መካን፡ ወአንከረ፡ ንጉሥ፡ ወእምድኅረዝ፡ ወከመ፡ ልማዶሙ፡ መጽኡ፡ ገዳመ፡ ንጉሥ፡ ከመ፡ ይንዳው፡ አራዊተ፡ ወረከቡ፡ ዓቢየ፡ አርዌ፡ ወወረው፡ ኲናቶሙ፡ ከመ፡ ይርግዝዎ፡ ወይቅትልዎ፡ ወጎየ፡ አርዌ፡ ወተሀብከ፡ ውስተ፡ ገዳም፡ ወተለዎ፡ ንጉሥ፡ ለአርዌ፡ እንዘ፡ ይጸአኑ፡ ፈረሶሙ፡ እንዘ፡ ይበጽሑ፡ ውስተ፡ ፈለግ፡ ቀዳሚ፡ ዘተረክበት፡ ቦቱ፡ ፈረስ፡ ንጉሥ፡ ረከበ፡ ፩ብእሲ፡ ጻድቅ፡ እንዘ፡ ይቤ፡ ወቆመ፡ ንጉሥ፡ ቅድሜሁ፡ ለመነኮስ፡ በፍርሐት፡ ወበርአድ፡ ወወረደ፡ ንጉሥ፡ ፈረሶሙ፡፡ ወተባረከ፡ በእዴሁ፡ ለመነኮስ፡ ወተአምን፡ በበይናቲሆሙ፡ ወይቤልዎ፡ ባህታዊ፡ ጻድቅ፡ ለንጉሥ፡ ለምኑ፡ መጻእከ፡ ወመኑመ፡ አምጻአከ፡ ኀበዝ፡ መካን፡ ወሜጠ፡ ንጉሥ፡ አንሰ ፡መጻእኩ፡ ከመ፡ እንዳው፡ አራዊተ፡ ወሶበ፡ መጻሕኩ፡ ረከብክዎ፡ በዝኩ፡ አርዌ፡ ወጎየ፡ ወአምስጠኒ፡ ወመጻእኩ፡ እንዘ፡ እተሉ፡ ኪያሁ፡ በአሠረ፡ እግሩ፡ ወአሜሃሰ፡ ሀሎ፡ አርዌ፡ ቀዊመ፡ እንዘ፡ ያሰምክ፡ በገቦሁ፡ ለመነኮስ፡ ጻድቅ፡ ከመ፡ ያድኅኖ፡ ወዜነውዎ፡ መነኮስ፡ ለፋሲለደስ፡ ንጉሥ፡ በከመ፡ ይደሉ፡ ብሔረ፡ መንግሥተከ፡ ነያ፡ ይእቲ፡ ሀገረ፡ ጎንደር፡ እንተ፡ ትውህዝ፡ ሀሊበ፡ ወመዓረ፡ ዘውእቱ፡ ሰላም፡ ወፍቅር፡ በውስቴታ፡ ብዙህ፡ መዝገብ፡ ወርቅ፡ ወብሩር፡ ዘውዕቱ፡ ትርጓሜ፡ ሐዲስ፡ ወብሉይ፡ ወይሰማዕ፡ በዕሌሃ፡ ማህሌተ፡ መላዕክት፡ ዘአርያም፡፡ወይቤ፡ ዳግመ፡ ባህታዊ፡ ጻድቅ፡ ወተሐንጽ፡ ቤተ፡ መንግሥትከ፡ በዲበ፡ ዛቲ፡ መካን፡ ወበአውዳ ተሐንጽ ብዙሐተ አብያተ ክርስቲያናት ወይቤ ንጉሥ እፎ እክለ ሐኒፆታ ለቤተ መንግስትየ በዲ ዝንቱ ፈለግ ወይቤ፡ መነኮስ፡ ጻድቅ፡ አስተጋብዕ፡ መነኮሳት፡

ገዳማዊያን፡ እለ፡ ሀለው፡ በገዳማት፡ ትግራይ፡ ወአምሐራ፡ ወይጸልዩ፡ ላዕለ፡ ፈለግ፡ ዘይውህዝ፡ ወአም፡ አሜሃ፡ ይየብስ፡ ማይ፡ ወትረክብ፡ ወጸለዩ፡ መነኮሳት፡ ፴መዓልት፡ ወ፴ሌሊት፡ በየብሳ፡ ማይ፡ ውስቴቱ፡ እብነ፡ ስፔር፡ ክቡር፡ ወመርግደ፡ ወቦቱ፡ ሕንጽ፡ ቤተ፡ መንግሥት፡ እንዘ፡ ይብል፡ ይኩነኒ፡ በከመ፡ ትቤለኒ፡ ወተመይጠ፡ ንጉሥ፡ በፍስሐ፡ ወበሰላም፡ ወእምድኅረዝ፡ ገብረ፡ በዓለ፡ ፯ዕለተ፡ እም፡ ብዙህ፡ ፍስሐ፡ ሐመ፡ ወገብአ፡ መንገለ፡ ዛቲ፡ መካን፡ ዘትሰመይ፡ ጎንደር፡ ወተክለ፡ ደብተራ፡ ወእምዝ፡ ሐነጸ፡ ቤተ፡ መንግሥቱ፡ ምስለ፡ ብዙኃት፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ በአምሳለ፡ ሕንጼሃ፡ ለደብረ፡ አንጾኪያ፡ ዘውእቱ፡ ቆማ፡ ፋሲለደስ፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት

ለይኩን ብርሃኑ፡፡ 1998፡፡<u>የግዕዝ መማርያ</u> ፡፡ዋሽንግተን ዲሲ፡፡ሲግኔቸር ማተሚያ ቤት፡፡

ዘርዓ ዳዊት አድኀኖ፡፡ 2002፡፡ <u>መርኆ ሰዋስው ዘልሳነ ግዕዝ</u>፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ዜና ማርቆስ እንዳለው ፡፡1955፡፡ <u>የግእዝ ቋንቋ መግቢያ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ሊቀ ኅሩያን በላይ መኰንን፡፡ 2002፡፡ ሕ<u>ያው ልሳን፡ግዕዝ-አማርኛ መዝገበ ቃላት</u>፡፡ አ.አ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፡፡ 1988፡፡ <u>ሀገረ መጽሕፍት</u>፡፡ አ.አ፡፡ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡1948፡፡ <u>መጽሐፈ፡ሰዋስው፡ ወግስ፡ ወመዝገበ፡ ቃላት፡ ሐዲስ፡፡</u> አ.አ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

አለማየሁ ሞገስ፡፡ (1950)፡፡<u>ሰዋስው ግዕዝ፡፡</u> አዲስ አበባ፡፡ ተስፋ ማተሚያ ቤት፡፡

አድማሱ ጀምበሬ /መልአከ ብርሃን/፡፡ 1963፡፡ <u>መጽሐፈ ዝክረ ሊቃውንት፣</u> አ.አ፡፡

ደስታ ተክለወልድ፡፡ 1946፡፡ <u>ረብሐ ስም ወአንቀጽ፡፡</u> አ.አ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

ደሴ ቀለብ፡፡ 2006፡፡ <u>ትንሣኤ ግእዝ</u>፡፡ አ.አ፡፡ አፍሮ ማተሚያ ቤት፡፡

ያሬድ ሽፈራው /ሊቀ ሊቃውንት/፡፡ 2007፡፡ <u>መጽሐፈ ግስ ወሰዋስው መርኆ መጽሐፍት</u>፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ጥቁር ዓባይ ማተሚያ ቤት፡፡

ተስፋ ገብረስላሴ፡፡ 1982፡፡ መጽሐፈ ሰዋስው መጽሔት አእምሮ፡፡ አ.አ፡፡ ተስፋ ገብረ ስላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ከኢ.ት/ያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አ/አ ዩኒቨርሲቲ፡፡ 1980፡፡ <u>የግእዝ ቅኔያት የስነ ጥበብ ቅርስ ንባቡ ከነትርጓሜው</u>፡፡አ.አ፡፡ የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስተር፡፡

ያሬድ ፈንታ፡፡ (1986) ፡፡ <u>ፍኖተ ግዕዝ</u>፡፡ አስመራ፡፡ ፍራንቺስካና ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታቸው ኀይሌ፡፡ (2008)፡፡ <u>ግዕዝ በቀላሉ ከናሙና ድርሰቶቹ ጋራ</u> ፡፡አ.አ፡፡ ማስተር

## ማተሚያ ቤት፡፡

Ayele Bekerie (1997). *Ethiopic: An African Writing System--Its history and principles.* Asmara, Eritrea: Red Sea Press.

Amsalu Tefera (2014). Introduction to Ethiopian philology. Addis Ababa. Unpublished.

(2015) Structure of Gəʿəz. Addis Ababa. Unpublished.

Bausi et al. (2015). *Comparative Oriental Manuscript Studies An Introduction.* Hamburg, Tredition.

Dillmann, August (2005). Ethiopic Grammar:2nd edition . Manufactured in the U.S.A. Wipf & Stock Publishers.

Leslow, Wolf (1991) Comparative Dictionary of Gəʿəz (Classical Ethiopic). Otto Harrassowitz, Wiesbades.

(1987). Conscience Dictionary of Gəʿəz. Wiesbaden: Harvessawitz.

Sergew HbleSellasse (1972). Ancient and Medieval Ethiopian history to 1270. Adds Ababa: United printing press.

Taddesse Tamrat. (1972). *Church and State in Ethiopia 1270-1527.*oxfored: oxford University press.